# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 190 መጋቢት 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ንግድ ባንክ ያጋጠመው ችግር

## በአገልግሎት ማሻሻያ ወቅት በተፈጠረ ክፍተት የተከሰተ እንጂ የሳይበር ጥቃት አለመሆኑን አስታወቀ

### - ችግሩ ከደንበኞች ሂሳብ ጋር ምንም ግንኙነት እንዳልነበረውም ተገልጿል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ መጋቢት 6 ቀን 2016 ዓ.ም ሌሊት የደረሰው ጉዳት ሲካሄድ የነበረውን የአገልግሎት ማሻሻያ ተከትሎ የተፈጠረ እንጂ በባንኩ ላይ የደረሰ የሳይበር ጥቃት አለመሆኑን የባንኩ ፕሬዚዳንት አቤ ሳኖ አስታወቁ፡፡ ችግሩ ከደንበኞች ሂሳብ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳልነበረውም አስታውቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቤ ሳኖ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ባንኩ በችግር ውስጥ በቆየባቸው ሰዓታት ከ490 ሺህ በላይ የገንዘብ ልውውጥ የተካሄደ ሲሆን፤ ሌሊቱን ሙሉ ግብይት ሲፈጸምባቸው የነበረባቸው የባንክ ሂሳቦች በሙሉ እስኪጣራ ድረስ እንዲታገዱ ተደርጓልም ብለዋል።

አቶ አቤ እንደገለጹት፤ ችግሩ የገጠመው የአገልግሎት ማሻሻያ ለመተግበር በተደረገ ሥራ ላይ በገጠመ ክፍተት እንጂ በማህበራዊ ሚዲያው እንደሚናፈሰው የሳይበር ጥቃት አይደለም፡፡

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ችግሩ የተከሰተውም አንድ የሂሳብ ማስታረቅ ሥራ ቅልጥፍና እንዲያመጣ ታስቦ የተሠራ የሲስተም ማሻሻያ ሲተገበር ስሕተት በመፈጠሩ ለሌቦች ቀዳዳ በመከፈቱ ነው፡፡


ንግድ ባንክ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፕሬዚዳንት አቤ ሳኖ

ፎቶ - በገባቦ ገብሬ






# የግብርና ኢንሹራንስ ለምን አልተስፋፋም?

**ሞገስ ጸጋዬ**

የኢትዮጵያ የግብርና መድህን (ኢንሹራንስ) ሽፋን አንድ ነጥብ አምስት በመቶ አካባቢ መሆኑ ይገለጻል፡፡ በኢትዮጵያ ከአስር በላይ የመድህን (ኢንሹራንስ) ኩባንያዎች ቢኖሩም የግብርና መድህን ሽፋን የሚሰጡት አራቱ ብቻ


የግብርና ኢንሹራንስ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አቶ አበሩ ጠና

# ለመጪው ክረምት

## እስካሁን 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- ለአረንጓዴ አሻራ ልማት እስካሁን አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች መዘጋጀታቸውን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ደን ልማት የአረንጓዴ አሻራና ሰው ሰራሽ ደን መሪ ስር አስፈጻሚ አቶ አበሩ ጠና በተለይ


ለመጪው ክረምት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# ኢትዮጵያና ስዊዘርላንድ

## በንግድና ኢንቨስትመንት ያላቸው ትብብር እያደገ መጥቷል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያና ስዊዘርላንድ በንግድና ኢንቨስትመንት ያላቸው ትብብር እያደገ መምጣቱን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ አስታወቁ፡፡

የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ እና የስዊዘርላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኢግናስዮ ካሲስ በትናንትናው ዕለት በተለያዩ የሀገራቱ የሁለትዮሽና በዓለም አቀፍ ግንኙነት ዙሪያ ተወያይተዋል፡ ከውይይቱ በኋላ የጋራ መግለጫ ሰጥተዋል።

ከውይይቱ በኋላ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ እንደገለጹት፤ የሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ያስቆጠረና ጠንካራ ነው፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያና ስዊዘርላንድ በንግድና ኢንቨስትመንት ያላቸው ትብብር እያደገ መጥቷል፡፡ በሁለቱ ሀገራት መካከል ቀደም ሲል የተደረሱ የትብብር ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግም መክረናል ብለዋል፡፡



ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ ስዊዘርላንድ በንግድና ኢንቨስትመንት ያላቸው ትብብር እያደገ መጥቷል ያሉት አምባሳደሩ፤ ሁለቱ ሀገራት ጠንካራ የንግድ ልውውጥ አላቸው፡፡ በርካታ የስዊዘርላንድ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ኢንቨስት እያደረጉ ነው። ስዊዘርላንድ ለኢትዮጵያ ትልቅ የገበያ መዳረሻ መሆኗን በመጥቀስ መሰል የንግድ ልውውጥ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

በቀጣይ የሁለቱን ሀገር የንግድ ልውውጥ ማጠናከርና ማሳደግ ይገባል ያሉት አምባሳደር ታዬ፤ በተለያዩ ጉዳዮች


ኢትዮጵያና ስዊዘርላንድ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ዜና

# በ2015/16 የምርት ዘመን 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ጥጥ ተመርቷል

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- በ2015/16 የምርት ዘመን ከ81 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ጥጥ ማምረት መቻሉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የጥጥ ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሳምሶን አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015/16 የምርት ዘመን 105 ሺህ ሄክታር መሬት በጥጥ ምርት ለመሸፈን ታቅዶ የተሠራ ሲሆን፤ 81 ሺህ ሄክታሩን መሬት ማልማት ተችሏል፡፡ በዚህም አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል የጥጥ ምርት ተሰብስቧል፡፡

የአማራ ክልል የጥጥ ልማቱ ሰፊውን ድርሻ የሚወስድ ነው ያሉት አቶ ሳምሶን፣ በተጨማሪም በደቡብ ኢትዮጵያና በተወሰነ ደረጃም ኦሮሚያ ክልል የጥጥ ልማቱ የተከናወነባቸው ክልሎች ናቸው ብለዋል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ፍላጎት አቅርቦት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ ቢሆንም፤ ትርፍ ምርት በማምረት ወደ ውጪ በመላክ ሀገሪቱ ተጨማሪ ውጪ ምንዛሬ እንድታገኝ የሚያደርግ ሥራዎችም ይሠራሉ ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ በዚህም በስድስት ወር ውስጥ ከነበረው ትርፍ ምርት ላይ 734 ቶን የተዳመጠ የጥጥ ምርት ወደ ተለያዩ ሀገራት በመላክ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ የአሜሪካ ዶላር ማግኘት ተችሏል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የጥጥ ምርት ከ60 በላይ ለሚሆኑ ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያገለግል በመሆኑ ምርቱን እሴት በመጨመር ወደ ውጪ የመላክ ሥራ በቀጣይ የሚሠራ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ሳምሶን ገለጻ፤ በዘንድሮው ዓመት የኢንዱስትሪዎች የጥጥ ፍላጎት መጠን 39 ሺህ ቶን የተዳመጠ ጥጥ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ፍላጎቱ በጣም መቀነሱን ነው፡፡

በምርት ዘመኑ የተመረተው የጥጥ ምርት ወደ ተዳመጠ ጥጥ ሲቀየር 57 ሺህ ቶን ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ በዚህም በሀገሪቱ በዚህ ሰዓት ከ15 ሺህ ቶን በላይ የተዳመጠ ትርፍ ጥጥ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

የዘንድሮ ዓመት የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች የጥጥ ፍላጎት የቀነሰ ቢሆንም አጠቃላይ የሀገሪቱ የጥጥ ፍላጎት ግን 105 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ ነው ያሉት አቶ ሳምሶን፤ ይህም የሆነው ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅማቸው በተለያዩ ሀገራዊ ምክንያቶች በመቀነሱ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ሳምሶን አሁን ላይ በሀገሪቱ እየተመረተ ያለው ምርት ኢንዱስትሪዎች በሙሉ አቅማቸው ወደ ማምረት ቢገቡ የጥጥ እጥረት እንደሚያጋጥም አንስተው፤ ከውጪ የሚመጣበት ሁኔታም ሊፈጠር እንደሚችል ጠቁመዋል።

"ይህን ያህል ትርፍ ጥጥ አለ ማለት ሀገሪቱ በጥጥ ምርት ራሷን ችላለች ማለት አይደለም ፡፡ እስካሁንም ከአጠቃላይ የኢንዱስትሪዎች የጥጥ ምርት ፍላጎት በሀገር ውስጥ እየተመረተ ያለው 50 በመቶ ብቻ ነው" ሲሉ አክለዋል፡፡



# የደሴ ከተማ መናኸሪያ ከአንድ ወር በኋላ ለአገልግሎት ክፍት ይደረጋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በ71 ሚሊዮን ብር ወጪ እድሳት የተደረገለት ነባሩ የደሴ ከተማ መናኸሪያ ከአንድ ወር በኋላ ለአገልግሎት ክፍት እንደሚሆን የደሴ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡

በአስተዳደሩ የከተማ እና መሠረተ ልማት ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ አብዱልከሪም ሀብታሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ 71 ሚሊዮን ብር የታደሰው ነባሩ የደሴ ከተማ መናኸሪያ ከአንድ ወር በኋላ ለአገልግሎት ክፍት ይሆናል፡፡

እንደ አቶ አብዱልከሪም ገለጻ፤ ነባሩ መናኸሪያ ዲዛይንና አስፓልት በመሥራት ለተሽከርካሪዎችና ለማህበረሰቡ ምቹ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፡፡

ቀደም ሲል የነበረው መናኸሪያ በ4 ሺህ ካሬ ሜትር ብቻ አገልግሎት እንደሚሰጥና የተቀረው የቆሻሻ መጣያ እንደነበር የገለጹት አቶ አብዱልከሪም፤ይኸው መናኸሪያ በአሁኑ ጊዜ 12 ሺህ ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን፤ ከአራት ሺህ በላይ ተሽከርካሪዎችን ያስተናግዳል ብለዋል።

ነባሩ የደሴ ከተማ የተሽከርካሪዎች መናኸሪያ ጽዱና ምቹ ያልነበረ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አብዱልከሪም፤ በክረምት በጭቃ ምክንያት ተሽከርካሪዎች እየተንሸራተቱ የሰው ሕይወት የሚያልፍበት ሁኔታ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

የመናኸሪያው እድሳት የደሴ ከተማን ገጽታ የቀየረ ትልቅ ፕሮጀክት መሆኑን ገልጸው፤ ከተማ አስተዳደሩ ዕድሳቱን ሙሉ በሙሉ አጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ማህበረሰቡም ከመናኸሪያው አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን በጉጉት እየተጠባበቀ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

ቀደም ባሉት ጊዜት ኅብረተሰቡ የተሽከርካሪ ትኬት ለመቁረጥ ውክቢያ ይገጥማቸው እንደነበር ጠቁመው፤የመናኸሪያው ዕድሳት ተጠናቀቆ ሥራ ሲጀምር የሀገር አቋራጭ፣ መለስተኛ ሚኒባሶች ተለይተው በዘመናዊ ሥርዓት መንገድ የሚስተናገዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል ብለዋል፡፡

በግቢው ውስጥ መብራት የተዘረጋ በመሆኑ ኅብረተሰቡ ለሌቦች በማይጋለጥበት መንገድ እንደሚስተናገድ በመግለጽ፤ ከመናኸሪያው መውጫ የሚገኘውን መንገድ አስፓልት የማልበስ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

በመናኸሪያው ወደ አገልግሎት አለመግባት ሳቢያ በተሽከርካሪዎች የትራፊክ መጨናነቅና ኅብረተሰቡም ለእንግልት መዳረጉን ገልጸው፤ የአስፓልት ሥራውን በሁለት ሳምንት ውስጥ በማጠናቀቅ ወደ አገልግሎት እንደሚገባም ተናግረዋል።

ከተማዋ የንግድ ማዕከል በመሆኗ ከፍተኛ መጨናነቅ እንዳለ ጠቅሰው፤ የተሠራው የመንገድና የመናኸሪያ ሥራ የከተማዋን የትራፊክ መጨናነቅ እንደሚያስቀር ተናግረዋል፡፡

# ሆስፒታሉ ለሰባት ሺህ ጨቅላ ሕፃናት አገልግሎት ሰጥቷል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ሆስፒታሉ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ለሰባት ሺህ ያህል ጨቅላ ሕፃናት የሕክምና አገልግሎት መስጠቱን የአበበች ጎበና የእናቶችና ሕፃናት ሆስፒታል አስታወቀ።

በሆስፒታሉ የሕፃናት ሕክምና ስፔሻሊስት ሐኪምና ሜዲካል ዳይሬክተር ዶ/ር ዱሬቲ ጀማል ለኢፕድ እንደገለጹት፣ ሆስፒታሉ ለእናቶችና ሕፃናት በተሻለ ሁኔታ የተሟላ የሕክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

አገልግሎት ከጀመረ ሦስት ዓመታትን ያስቆጠረው ሆስፒታል በየወሩ በአማካይ 250 ጨቅላ ሕፃናት ይታከማሉ።


ዳይሬክተሯ እንደተናገሩት፣ ከተወለዱ ከ28 ቀናት በታች ለሆኑና ሕክምና ለሚያስፈልጋቸው ጨቅላ ሕፃናት በተዘጋጀላቸው 60 የአስተኝቶ ማከሚያ አልጋዎች የሕክምና አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ከ2ኪሎ በታች ሆነው ለሚወለዱ ጨቅላ ሕፃናትም በራሱ የማሞቂያ ክፍል እንክብካቤ እየተደረገላቸው የሚቆዩበት ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡

የጨቅላ ሕፃናት ላይ የሚገጥመው ሌላ ችግር ቢጫ ሆኖ መወለድ መሆኑን የጠቀሱት ዶ/ር ዱሬቲ፤ ለዚህም ሆስፒታሉ የፎቶ ቴራፒ ሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጥም አንስተዋል፡፡

ሆስፒታሉ ከሌሎች የመንግሥት ሆስፒታሎች በተለየ በራሳቸው መተንፈስ ለማይችሉ ጨቅላ ሕፃናትም በማሽን የመተንፈሻ አገልግሎት እንደሚሰጥም ገልጸዋል፡፡

ሆስፒታሉ በየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ስር መሆኑን ያስታወሱት ዶ/ር ዱሬቲ፤ የቀዶ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ጨቅላ ሕፃናት ሲኖሩ በሜዲካል ኮሌጁ ባሉ የሕፃናት ቀዶ ጥገና ስፔሻሊስቶች አማካኝነት የቀዶ ሕክምና እንደሚያገኙም አስታውቀዋል፡፡

እንደ መንግሥት የጨቅላ ሕፃናትን ሞት መቀነስ ትልቅ ትኩረት የተሠጠው መሆኑን ያስታወሱት ዶ/ር ዱሬቲ፣ ይህንን ለመተግበር አገልግሎት ፈላጊዎች ወደ ሌላ የሕክምና ተቋም የማይሄዱበትን ሰፊና የተሻለ አገልግሎት እየሰጠን ነው ብለዋል፡፡



ፎቶ - ዳኜ አበራ

**ዶ/ር ዱሬቲ ጀማል**

ሆስፒታሉ የሚሰጠውን አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳደገ በመምጣቱ በተለይም ያለጊዜያቸው የሚወለዱ ጨቅላ ሕፃናትን ሞት በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ መቻሉንም ተናግረዋል፡፡

ለሕክምና ከተኙ ጨቅላ ሕፃናት መካከል 85 ከመቶዎቹ ድነው መውጣት አለባቸው የሚል ሀገር አቀፍ እቅድ መኖሩን ጠቅሰው፣ ሆስፒታሉ አሁን ባለው አገልግሎት 90 ከመቶ ያህሉ ጨቅላ ሕፃናት ድነው እንዲወጡ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ሆስፒታሉ ከመንግሥት በሚሰጠው በጀት ብቻ የሚንቀሳቀስ መሆኑን የጠቀሱት ዶ/ር ዱሬቲ፤ ሠራተኛውና አመራሩ ባለው በጀትና አቅም የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚተጋ መሆኑ የተሻለ አገልግሎት መስጠት አስችሎታል ብለዋል፡፡

አበበች ጎበና የእናቶችና ሕፃናት ሆስፒታል የሕፃናት ተመላላሽ ሕክምና፣ የክትባትና የግርዛት አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን፣ ሕፃናት በተወለዱ በ90 ቀናቸው የልደት ሰርተፊኬት እንዲያገኙም ያደርጋል።

# የተጓዦችን ቅሬታ ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራን ነው

## - የኢትዮጵያ አየር መንገድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**




**አቶ መስፍን ጣሰው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከሰሞኑ በማኅበራዊ ሚዲያ እየተዘዋወሩ ያሉ የተጓዦችን ቅሬታ ለመፍታት እየሠራ መሆኑን የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መስፍን ጣሰው ገለጹ፡፡

የደንበኞችን እርካታ ለማስፋት ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራን ነው ያሉት አቶ መስፍን፤ በማኅበራዊ ሚዲያ እየተዘዋወሩ ያሉ ችግሮች መኖራቸውን ብናስተውልም የተገለጹበት መንገድ ግን የተጋነነ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አየር መንገዱ ተደራሽነቱን በማስፋት እና የመሠረተ ልማትን የበለጠ በማጠናከር ዘርፉ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተሻለ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ከሰሞኑ በማኅበራዊ ሚዲያ የተነሱ ቅሬታዎችን እየመረመርን ነው ያሉት አቶ መስፍን፤ ለአብነትም አንድ ሠራተኛ ዶላር እና ሌሎች ዕቃዎችን በጉቦ መልክ ሲጠይቅ በአየር መንገዱ ካሜራ ሊታይ እንደተቻለም ጠቁመዋል፡፡

በዚህም በተደረገ ማጣራት፤ ግለሰቡ በአየር መንገዱ ጥምር አገልግሎትን ከሚሰጡ መሥሪያ ቤቶች አንዱ የሆነው የጉምሩክ ኮሚሽን ሠራተኛ መሆኑን በማረጋገጥ በቁጥጥር ስር ሊውል እንደቻለ ተናግረዋል።

አቶ መስፍን አያይዘውም፤ በመሥሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በተገጠሙ የደህንነት ካሜራ በመታገዝ ሌሎች ተያያዥ የሥነ-ምግባር ችግር ያለባቸው ሠራተኞች ላይ ከአስተዳደራዊ ቅጣት ለሕግ እስከማቅረብ የደረሰ እርምጃ እንደሚወሰድም ገልጸዋል፡፡

ይህን መሰል ችግር ለመከላከል አዲስ አሠራር እየተዘረጋ ነው ያሉት አስፈጻሚው፤ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በየወሩ የተሠሩ ሥራዎችን የምንፈትሽበት ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል።

አክለውም ማንኛውም መንገደኛ ብልሹ አሠራር በሚገጥመው ወቅት፤ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ሳይሆን እዚያው ቅሬታውን አስገብቶ መፍትሄ የሚገኝበት ይሆናል ብለዋል፡፡

የአየር መንገዱን የደንበኞች አገልግሎት ይበልጥ ምቹና ቀልጣፋ ለማድረግ የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመላክተዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት በስድስት አዳዲስ ዓለም አቀፍ መዳረሻዎች ለመብረር አቅዶ እስካሁን ሦስቱን ማሳካቱን ጠቅሰዋል።

በአውሮፕላን ግዥም ስምንት አውሮፕላኖችን ለመግዛት ታቅዶ እስካሁን የስድስት አውሮፕላን ግዥ መሳካቱን ገልጸዋል።

በቀጣይነትም የ124 አውሮፕላኖች የግዥ ትእዛዝ መኖሩን ጠቁመው፤ ከመሠረተ ልማት አንጻርም የኢ-ኮሜርስ ፋሲሊቲ፣ የኃይል አቅርቦት ሰብስቴሽን እንዲሁም የሀገር ውስጥ በረራ ተርሚናል ግንባታ ተጠናቆ ሥራ መጀመሩን ገልጸዋል።

በግንባታው ዘርፍ የተርሚናል ሁለት ማስፋፊያ መደረጉን አንስተው፤ አሁን ላይ ተጨማሪ የማስፋፊያ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑንም ተናግረዋል።

ከደንበኞች አገልግሎት ጋር በተያያዘ በተመዘገበው ስኬት አየር መንገዱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ እውቅና እና ሽልማቶችን ማግኘቱንም ጠቅሰዋል።

በአገልግሎት አሰጣጡ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት የሚያስችሉ አዳዲስ አሠራሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ ሲሉ አቶ መስፍን አስታውቀዋል።

# እየተተገበረ የሚገኘው የሪፎርም ሥራ የተቋም ግንባታን ለመፍጠር ያለመ ነው

## - የሪፎርም ሥራው የዝግጅት ምዕራፍ በማጠናቀቅ ወደ ትግበራ ምዕራፍ ተሸጋግሯል

**ማህሌት ብዙነህ**



**ጣሰው ገብሬ (ዶ/ር)**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በ16 ተቋማት ላይ የተካሄደው የሠራተኞች የሪፎርም ሥራ የተቋም ግንባታን ለመፍጠር ያለመ መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ገለጸ። በሪፎርም ሥራው የዝግጅት ምዕራፍ በማጠናቀቅ ወደ ትግበራ ምዕራፍ መሸጋገሩም ተጠቁሟል፡፡

በአዲስ አበባ በ16 ተቋማት ላይ የተካሄደው ሪፎርም ተግባራዊ መደረግ መጀመሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በትናንትናው እለት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል፡፡

የቢሮው ኃላፊ ጣሰው ገብሬ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ በከተማዋ በሚገኙ 16 ተቋማት ላይ የሪፎርም ሥራ ማካሄድ ያስፈለገበት ምክንያቶች መካከል የተጠያቂነት ሥርዓት አለመኖር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር፣ የብቃት ማነስ እና የሥራና ሠራተኛ አለመመጣጠን ይገኙበታል፡፡

ሪፎርሙ ትኩረት ያደረገባቸው የቴክኖሎጂ፣ የመዋቅራዊ አደረጃጀት ሥራ፣ እንዲሁም የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያዎችንና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ግንባታ ተግባራዊ ማድረግ ላይ እንደሆነም አስታውቀዋል።

በዝግጅት ምዕራፉ ላይ የአሠራር ሥርዓት ለማሻሻል፣ የደንብና መመሪያ ዝግጅት መደረጉን አመልክተው፤ የቴክኖሎጂ ልየታና ዝግጅት ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን፤ በዚህም 42 አዳዲስ የአይሲቲ መሠረተ- ልማቶች ወደ ሥራ እንደሚገቡ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በሦስተኛ ወገን የሚሠሩ አገልግሎቶችና ተቋማት የመለየት እንዲሁም ከ19 ሺህ በላይ የአመራሮችና ሠራተኞች ባህሪያዊ እና ቴክኒካል ብቃትን ለመለካት ፈተና የወሰዱ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ፈተናውን ያለፉና ብቁ የሆኑ ሠራተኞችና አመራሮችም በየደረጃው ምደባ የተደረገላቸው መሆኑን ጣሰው (ዶ/ር) ተናግረዋል።

ከእነዚህም ውስጥ 33 ነጥብ 3 በመቶ አመራር እንዲሁም 50 ነጥብ 6 በመቶ ባለሙያዎች ያለፉ ሲሆን፤ የተሰጠውን ፈተና ካለፉት ውስጥም 99 ነጥብ 9 በመቶ የሚሆኑ ዳይሬክተሮችና ሥራ አስተባባሪዎች፣ 88 በመቶ ቡድን መሪ እንዲሁም 88 በመቶ ባለሙያዎች ድልድል በመስፈርት መሠረት የተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ፈተናውን ያላለፉ ደግሞ ከ2 ደረጃ ዝቅ በማለት መመደባቸውን እንዲሁም ሠራተኞችን ለማመጣጠን ወደ ክፍለ ከተማና ወረዳ ምደባዎች መካሄዳቸውንም ኃላፊው አስታውቀዋል፡፡

የባህሪ ግንባታ እና ትግበራ ክህሎት ላይ ያተኮረ ስልጠና ከ17 ሺህ በላይ ሠራተኞች ስልጠና መውሰዳቸውም ተመልክቷል።

በከተማዋ የሚገኙ 16 ተቋማት የሠራተኞች ምዘናና ምደባ የሪፎርም ሥራ ተጠናቆ ወደ ትግበራ ምዕራፍ መግባቱንም ገልጸዋል።

በዚህም አገልግሎትን በማሳለጥ የተገልጋዩን የእርካታ ደረጃ ከፍ በማድረግ በነጻነት እንዲገለገል ለማስቻል እና ከብልሹ አሠራር የጸዳ ለማድረግ የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ቢሮው ከዝግጅት ምዕራፍ ወደ ተግባር ምዕራፍ መሸጋገሩን ገልጸው፤ ለተግባራዊነቱ በተለይም አመራሩ እገዛ ማድረግ እንዳለበትም ጣሰው (ዶ/ር) አስታውቀዋል፡፡



**ደረጄ ዱጉማ (ዶ/ር)**

# በኢትዮጵያ 52 በመቶ ሞት የሚከሰተው ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ 52 በመቶ የዜጎች ሞት የሚከሰተው ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የተነሳ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ለማጠናከር ያለመ አውደ ጥናት በጤና ሚኒስቴርና በላስት ማይል ሄልዝ አማካኝነት ተካሂዷል፡፡

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ደረጀ ዱጉማ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ጫና ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ በሆስፒታል አልጋ ይዘው ከሚታከሙ ታማሚዎች 80 በመቶ የሚሆኑት ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የተያዙ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ከሚከሰቱት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ግፊት፣ ስኳር፣ የልብ ህመም፣ ካንሰር እና የአዕምሮ ጤና እክል ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ጠቅሰዋል።

ባለፉት ዓመታት ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ እንደነበር የገለጹት ዶክተር ደረጀ፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት በእናቶች ጤናና በሕፃናት ሞት ላይ ትኩረት ተደርጓል፤ ይህም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል አዳጋች ሆኗል ብለዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳመለከቱት፤ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ጫና እያደረሱ ይገኛል፡፡ በዓለም ከሚከሰት 57 ሚሊዮን ሞት 71 በመቶ የሚሆነው ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ነው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ከሚከሰት ሞት ከ70 እስከ 80 በመቶ የሚከሰተው ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው እንደተናገሩት፤ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ ያለው የማህበረሰቡ ግንዛቤ ውስን በመሆኑ ሰፊ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል።

ሰዎች ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የተነሳ አካላዊና አዕምሯዊ ጉዳት ከደረሰባቸው በኋላ ወደ ጤና ተቋማት እንደሚመጡ ጠቁመው፤ ይህ ደግሞ የጤና ችግር ብቻ ሳይሆን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት እያስከተለ መሆኑን ገልጸዋል።

የጤና ሚኒስቴር አሁን ላይ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ምርመራ በማድረግና አመጋገብን በማስተካከል መከላከል ይቻላል፤ በዚህም ግለሰቡ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡና መንግሥት ተጠቃሚ ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ዶክተር ደረጄ እንደገለጹት፤ ከአንድ ሺህ 200 በላይ የሚሆኑ ጤና ተቋማት የማህጸን በር ካንሰር ምርመራና ሕክምና እየሰጡ ይገኛል፡፡ በአንድ ዓመት ከ750 ሺህ በላይ የማህጸን በር ካንሰር ልየታ ተደርጓል፡፡

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል የተቋሙ ቀዳሚ ዓላማ በመሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ወደ ማህበረሰቡ ቤት በመሄድ የቅድመ ምርመራና የምክር አገልግሎት እንደሚሰጡ አመልክተዋል።

እስካሁን ድረስ ለአራት ሺህ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ በዘንድሮ ዓመት አንድ ሺህ 500 ጤና ኤክስቴንሽኖችን ለማሰልጠን ታቅዷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# ንግድ ባንክ ያጋጠመው ችግር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባንካቸው ጠንካራና የተሻለ ምስጢራዊ ሥርዓት “ሴኩሪቲ ሲስተም” ካላቸው ተቋማት መካከል አንዱ መሆኑን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች ትኩረት ቢያደርጉበትም አንድም ተቋም ግን የባንኩን የሳይበር ሴኩሪቲ ሲስተም አልፎ ሊያጠቃ አለመቻሉን ጠቅሰዋል።

የተፈጠረው ችግር ለተለያዩ ሌቦችና ላልተገባ ተግባር አጋልጦናል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህም እጅግ በጣም ያስደነገጠንና ያሳዘነንም ነገር ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ በንግግራቸው፤ በበጀት ዓመቱ የስምንት ወር የባንክ እንቅስቃሴ የዲጂታል አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር 32 ሚሊዮን ያለፈ ሲሆን፤ ጠቅላላ የተፈፀመ የሂሳብ ዝውውር መጠን ደግሞ በቁጥር 800 ሚሊዮን እና በገንዘብ መጠን ደግሞ ብር 10 ትሪሊዮን ነው ብለዋል።

ይህ የዲጂታል የሂሳብ እንቅስቃሴ ባንኩ ካከናወናቸው ጠቅላላ እንቅስቃሴዎች 73 በመቶውን የሚሸፍን ሲሆን፤ በቀን ውስጥ ከአራት ሚሊዮን የሚበልጡ ደንበኞችን ያስተናግዳል። በየዓመቱ የዲጂታል የገንዘብ ዝውውር ቁጥር እየጨመረ የመጣ ሲሆን፤ አምና ከነበረበት ተመሳሳይ ወቅት አንፃር በዚህ ዓመት የ150 ሚሊዮን (16 በመቶ) ለውጥ አሳይቷል ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ የትኛውም አቅጣጫ የሚገኙ ሁሉም ቅርንጫፎች በኮር ባንኪንግ ቴክኖሎጂ የተሳሰሩ በመሆናቸው እና የዲጂታል አማራጮቹም ከዚሁ ሲስተም ጋር በቅንጅት የሚሠሩ ስለሆኑ አገልግሎቶቻችን በሙሉ ያለምንም ችግር በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ ለደንበኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ደህንነቱ የተጠበቀ አሠራር መኖሩ ግድ እንደሆነ ያምናልም ነው ያሉት።

ለዚህም ከመረጃ መረብ ጥቃት የፀዱ እንዲሆኑ ባንኩ በትጋት በቀን 24 ሰዓት በሳምንት 7 ቀን ያለማቋረጥ በመሥራት ላይ ሲሆን፤ የመረጃ መረብ ጥቃት እንዳይከሰት የመከላከል ሥራ፣ የሚገኙ የጥቃት ዓይነቶችን በየፈርጁ በመለየት የምርምር፣ ትንተና እና ትንበያ ሥራ ይሠራል ብለዋል፡፡

በባንኩ ኢ-ሜይል እና በቀጥታ የባንኩ የተለያዩ ሲስተሞች ላይ የሚካሄዱ የሳይበር ጥቃቶችን በመለየት ከመረጃ መረብ ደህንነት አስተዳደር እና ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር በመተባበር እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል ብለዋል።

የሲሲተም ማሻሻያዎችንም ትኩረት በመስጠት እና ጥንቃቄ ተጨምሮበት የሚቀጥል መሆኑን ያረጋገጡት ፕሬዚዳንቱ፤ በባንኩ ላይ የደረሰው ጉዳት ከባንኩ አቅምና ሀብት አንጻር እጅግ በጣም አነስተኛ ሊባል የሚችል በመሆኑ በባንካችን ላይ የሚያደርሰው የጎላ ተፅእኖ የለም ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እስካሁን ምን ያህል ጉዳት ደርሷል የሚለው ተጠንቶ ስላላለቀ ሲያልቅ ይፋ እንደሚደረግ አመልክተዋል። ስለሆነም ጉዳዩን በሚመለከት በማህበራዊ ሚዲያ የሚተላለፉ አላስፈላጊና ሀሰተኛ መልዕክቶች ልክ ስላለመሆናቸውም ተናግረዋል።

በቀጣይ በደረሰው ጉዳት ላይ ዝርዝር ምርመራ በማጠናቀቅ ጉዳት አድራሾች የወሰዱትን ገንዘብ በፈቃደኝነት እንዲመልሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ ይህም ካልተሳካ አፋጣኝ የሕግ እርምጃ መውሰድ በትኩረት የምንሠራው ተግባር ነው ሲሉ ተናግረዋል። በዚህ ጉዳዩ ላይ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ የጀመሩትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ባንኩ ችግሩ በተከሰተበት ወቅት ከ490 ሺህ በላይ የገንዘብ ልውውጥ መካሄዱን አቶ አቤ ጠቁመው፤ ሌሊቱን ሙሉ ግብይት ሲፈጸምባቸው የነበረባቸው የባንክ ሂሳቦች በሙሉ እስኪጣራ ድረስ እንዲታገዱ መደረጋቸውንም ገልጸዋል፡፡

# ኢትዮጵያና ስዊዘርላንድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አጋርነት ለማጠናከር በውይይቱ ወቅት መግባባት ላይ መደረሱን ጠቅሰዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ታዬ ማብራሪያ፤ በሁለትዮሽ፣ በቀጣናዊና በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ ውጤታማ ውይይት አድርገናል፡፡ በተለይ ድንበር ተሻጋሪ ሽብርተኝነት በመከላከልና በሱዳን ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ ውይይት ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት፣ የሽግግር ፍትህና ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የአፈጻጸም ሂደት ሌላው ውይይት ያደረጉባቸው መስኮች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ የፕሪቶሪያን የሰላም ስምምነት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኗን በውይይቱ ወቅት መገለጹን ጠቅሰዋል፡፡

የስዊዘርላንድ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኢግናስዮ ካሲስ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ፣ በኬንያና በጅቡቲ ለአራት ቀን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት እንደሚያደርጉ በመጥቀስ ከኢትዮጵያ መጀመራቸውን ገልጸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ማዕከል ናት፤ከአፍሪካ ሁለተኛው የሕዝብ ቁጥር ባለቤትና የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ በመሆኗ ለወደፊት የአፍሪካ አህጉር ወሳኝ ሚና እንደሚኖራት ይጠበቃል ብለዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያና ስዊዘርላንድ ጠንካራ የንግድ ግንኙነት አላቸው፡፡ 20 የስዊዘርላንድ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ተሰማርተው እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ ዓመታዊ የንግድ ልውውጡ አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ነው፤ አሁን ካለው አቅም አንጻር ማሳደግ ይገባል ብለዋል፡፡

ስዊዘርላንድ ወደ ኢትዮጵያ የኬሚካልና የፋርማሲ ውጤቶችን እየላከች ሲሆን፤ የቡናና ወርቅ ምርት ከኢትዮጵያ ወደ ስዊዘርላንድ እንደሚላክ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያና ስዊዘርላንድ በሁለትዮሽና በዓለም አቀፍ ጉዳዮች በጋራ እየሠሩ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በፍልሰተኞች፣ በሳይንስ ዲፕሎማሲ፣ በቀይ ባህር፣ በሩቅ ምሥራቅ ጉዳይ በጋራ እንሠራለን ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በሱዳን ሰላም እንዲሰፍን በጋራ እንደሚሠሩ በመግለጽ፤ የሰብአዊ እርዳታና የተኩስ አቁም ስምምነት መፍትሔ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

# ለመጪው ክረምት እስካሁን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ እስካሁን ለአረንጓዴ አሻራ ልማት አምስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የደን ችግኝ ሁለት ቢሊዮን እንዲሁም የቀርከሃ 60 ሚሊዮን የሚይዝ ሲሆን ቀሪው “የአግሮ ፎረስተሪ” ችግኞች ናቸው።

ለተከላ የተዘጋጁ ችግኞች ተብለው የሚለዩት ከሃያ አምስት ሴንቲ ሜትር በላይ ቁመትና ሊጸድቁ የሚችሉ መሆናቸውንም አብራርተዋል።

በአጠቃለይ በ2016 ዓ.ም ለሚካሄደው የሁለተኛ ምእራፍ ሁለተኛ ዙር የአረንጓዴ አሻራ ልማት ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች ለማዘጋጀት እቅድ የተያዘ ሲሆን፤ ቀሪው አንድ ቢሊዮን በአጭር ጊዜ ሊደርሱ የሚችሉት ችግኞች የሚዘጋጁበት ይሆናል ብለዋል።

ከአጠቃላይ የችግኝ ዝግጅቱ አርባ በመቶ የደን ችግኝ ሲሆን፤ ቀሪው ስልሳ በመቶ የአግሮ ፎረስተሪ ማለትም ለሰውና ለእንስሳት ምግብነት የሚውሉ አትክልት ፍራፍሬና የመኖ ችግኞች ናቸው።

በዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ ልማት እንቅስቃሴ ካሉት 99 ሺ 810 ችግኝ ጣቢያዎች ለ61 ሺ 810 ካርታ የማዘጋጀት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ያሉት አቶ አበሩ፤ ይህም የት እንዳሉ፤ ምን ያህል እያመረቱ እንደሆነና የዝግጅት አካሄዳቸውንም በቅርበት ለመቆጣጠር እንዲሁም በቋሚነት ለችግኝ ማፍያ የሚያገለግሉትን እና እንደ አዲስ ወደ ችግኝ ማምረት እየገቡ ያሉትን ለመለየት የሚያስችል ይሆናል ብለዋል።

በተጨማሪም ዘንድሮ ከእስካሁኑ በተለየ ከችግኝ ማዘጋጀት በተጓዳኝ 700 ሺ ሄክታር መሬት የመትከያ ቦታ ልየታ የሚሰራ ሲሆን፤ ለዚህም እስካሁን አራት መቶ ሺ 899 ሄክታር መሬት መለየቱንና ለ289 ሺ 869 ሄክታር ካርታ መዘጋጀቱን ጠቁመዋል። የቀረውም በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት የሚጠናቀቅ ይሆናል ብለዋል።

# የግብርና ኢንሹራንስ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ናቸው፡፡ የግብርና መድህን ሽፋን ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ አደሮች 150 ሺህ እንደማይሞሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የግብርና ገጠር ልማት ፖሊሲ ሲሻሻል የግብርና ኢንሹራንስ አንዱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ የግብርና ኢንሹራንስ መዋቅርና የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖረው እየተሠራ ሲሆን፤ የኢንሹራንስ ጠቀሜታን በተመለከተ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች በስፋት እየተሠሩ እንደሚገኙ የግብርና ሚኒስቴር ይገልጻል፡፡ የግብርና ኢንሹራንስ ለምን አላደገም? ችግሮቹ ምንድን ናቸው? እና እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በተመለከተ የዘርፉ ባለሙያዎች ሃሳባቸውን እንደሚከተለው አካፍለውናል።፡

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ኢንቨስትመንትና ምርት ግብይት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደረጄ አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ግብርና በዝናብ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ለተለያዩ ችግሮች የመጋለጥ እድሉ ሰፊ ነው፡፡ በግብርና ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቀነስ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው የግብርና ኢንሹራንስ አለመስፋፋቱ ጉዳት አለው፡፡

በተለያዩ ክልሎች የግብርና ኢንሹራንስ የሙከራ ሥራዎች ቢኖሩም በጣም አነስተኛ ነው ይላሉ፡፡

በኢትዮጵያ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ የግብርና ኢንሹራንስ በሙከራ ደረጃ ተፈጻሚ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ ዕድገት አላሳየም ያሉት አቶ ደረጀ፤ በአማራ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ የሀገሪቷ አካባቢና በኦሮሚያ ክልሎች ጥሩ ተሞክሮዎች አሉ፡፡ ያሉ ልምዶችን አስፍቶና ቀምሮ እንደ ሀገር የማስፋት ሥራ በቀጣይ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል ነው ያሉት፡፡

በኦሮሚያ ያለው ልምድ በሰነድ ደረጃ ተዘጋጅቷል፤ እንዲሁም የግብርና ኢንሹራንስ መመሪያ የተዘጋጀ በመሆኑ ለቀጣይ ሥራዎች አጋዥ ይሆናል ብለዋል፡፡

የተዘጋጀው የግብርና ኢንሹራንስ ሰነድ በግብርና ኢንሹራንስ ውስጥ የመንግሥት አበርክቶ ምን መሆን አለበት? የግል ድርጅቶች ምን ዓይነት ሁኔታዎች መሥራት አለበት? የግብር ኢንሹራንስ የሚደግፉ ድርጅቶች ሚና ምን መሆን አለበት? የሚልና በዚህ ዘርፍ ቢሰሩ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ እነማን ናቸው? የሚሉትን ያቀፈ ነው፡፡ ሰነዱ በቀጣይ በስፋት ታትሞ ለክልሎች እንደሚሰራጭ ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የግብርና ኢንሹራንስ ሽፋን አንድ ነጥብ አምስት በመቶ አካባቢ ነው የሚሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ይህ ብዙ እንዳልሠራን ያሳያል፡፡ በሀገር ደረጃ ያሉ የሙከራ ሥራዎች በተደረገ ፍተሻ አንዳንዶች በማበረታቻ ሌሎች ደግሞ ያለማበረታቻ የሚሠሩ ናቸው። በቀጣይ የትኛው አዋጭ ነው የሚለው ይለያል ብለዋል።

የግብርና ኢንሹራንስ ጠቀሜታን ለአርሶ አደሩ ማስረጽ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ደረጄ፤ አርሶ አደሮች ለግብርና ሥራቸው ኢንሹራንስ እንዲገቡ ግብርና ሚኒስቴር ትልቅ ሥራ እየሠራ ነው፡፡ የግብርና ኢንሹራንስ ሊሰፋ የሚችለው የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ሲሠራ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የግብርና ገጠር ልማት ፖሊሲ ሲሻሻል የግብርና ኢንሹራንስ አንዱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን ጠቁመው፤ በአስር ዓመት የግብርና እቅድ ውስጥም የግብርና ኢንሹራንስ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በቀጣይ የሕጋዊ ማዕቀፍ ፈጥሮ እስከ ቀበሌ ባለው መዋቅር ዘርፉን ለመደገፍ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡ መዋቅርና የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖረው በቀጣይ ይሠራል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

የፑላ ኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳግማዊ ኃይለየሱስ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የግብርና ኢንሹራንስ እንዳያድግ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል የአረቦን ክፍያ በአማካኝ አንድ ሺህ 600 ብር አካባቢ መሆን፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች አቅም አለማደግ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የግብርና ኢንሹራንስ እንደ ሌሎች ኢንሹራንስ ዓይነት ባለመሆኑ ካሳ ሲመጣ ክፍያው ትልቅ ነው፡፡

ይህን መሰል ችግር ለመጋፈጥ አቅም ያለው የኢንሹራንስ ኩባንያ አለመኖር እንዲሁም ያለው የግብርና



ኢንሹራንስ በውጭ ድጎማ ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ ድጎማው ሲቆም የአረቦን ድጋፍ ፕሮግራሙም አብሮ መውደቅ ሌላው የዘርፉ ችግር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ፑላ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሁለት ዓመት በፊት ሥራ መጀመሩን የገለጹት አቶ ዳግማዊ፤ ፑላ ዓለም አቀፍ የኢንሹራንስ ኩባንያ ሲሆን በ19 አካባቢዎች ይሠራል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ከሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚሆኑ የግብርና ምርቶችን የኢንሹራንስ ሽፋን ሰጥቷል ይላሉ፡፡

በረዶ፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ፣ የዝናብ ማነስ፣ ድርቅ፣ ተባይና የተለያዩ የሰብል በሽታዎችን አካቶ ኢንሹራንስ ሽፋን የሚሰጥባቸው መስኮች ላይ እየሠራ እንደሆነ ገልጸው፤ በኢትዮጵያ እስከ ዛሬ በነበረው ፕሮግራም ኢንሹራንስ የሚሸፍነው ድርቅን ብቻ በመሆኑ የአርሶ አደሮችን ሰብል አንበጣ ሲያወድመው የካሳ ክፍያ እንደማያገኙ ነው የተናገሩት፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የግብርና ኢንሹራንስ እንዳያድግና እንዳይስፋፋ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል የአረቦን ክፍያ ከፍተኛ መሆን ተጠቃሽ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ በግብርና ኢንሹራንስ ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ አደሮች ከ15 ሺህ አይበልጡም የሚሉት አቶ ዳግማዊ፤ ፑላ 120 ሺህ አርሶ አደሮች በኢትዮጵያ ትልቁ የሚባል የግብርና ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል፡፡ በቀጣይ ሦስት ዓመታት ውስጥ ሰባት ሚሊዮን አርሶ አደሮችን በስማርት ድጎማ አማካኝነት የኢንሹራንስ ተጠቃሚ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

የግብርና ኢንሹራንስ በኢትዮጵያ ከአስር ዓመት በፊት መጀመር ነበረበት የሚሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር የኢትዮጵያ የግብርና ኢንሹራንስ ያለበት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ የሚባል ነው፡፡ በኢትዮጵያ ከአስር በላይ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች አሉ፤ ነገር ግን አሁን ባለው የሥራ አካሄድ የግብርና ኢንሹራንስ የሚሰጡት አራቱ ብቻ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡

የግብርና ኢንሹራንስ የሕይወት ወይም እንደ ሌሎች ኢንሹራንስ ባለመሆኑ ካሳ ሲመጣ ክፍያው ከፍተኛ ነው። የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ለዚህ የሚሆን አቅም ያላቸው ባለመሆኑ ግብርና ኢንሹራንስ እንዳያድግ እንዳደረገው ገልጸዋል፡፡

በአየር ንብረት ለውጥ በድርቅ፣ በግጭት፣ በበረዶ፣ በሌሎች በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ሰብሎች በመሰብሰቢያቸው ወቅት ይወድማሉ፤ አርሶ አደሩም ተጎጂ ይሆናል፡፡ ይህን ለመከላከል አሠራርን በመዘርጋትና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ በመሥራት አርሶ አደሩን የግብርና ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል ነው ያሉት፡፡

ግብርና ሰፊ የሥራ እድል የሚፈጥርና የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ የኢኮኖሚ አለኝታ መሆኑን በመገንዘብ ለግብርና ኢንሹራንስ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በዘርፉ የሚሰማሩ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች አቅም በማሳደግ አርሶ አደሩ ሠርቶ ከኪሳራ ሊጠበቅ ይገባል ባይ ናቸው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕዝባዊ ውይይቶቹ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት አቅም ናቸው!

በአንድ ሀገር ውስጥ እንዲኖር የሚፈለግ ሰላም፣ እንዲመጣ የሚፈለግ ልማት፣ እንዲሰፍን የሚፈለግ የዴሞክራሲ ሥርዓት፤ በጥቅሉ እንዲሆን የሚጠበቅ ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን የሚሆነው የሰፊው ሕዝብ ይሁንታና ተሳትፎ ሲታከልበት ነው፡፡ በዚህ ረገድ እንደ ሀገር የሚከወኑ የልማት፣ የሰላምና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ይሳኩ ዘንድ ሕዝብን አወያይቶ የማሳተፍ አካሄዶች የተለመዱ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያም ከዘመናት ሂደት ውስጥ እንዲህ ዓይነት የሕዝብ ይሁንታና ተሳትፎን በሚሹ ጉዳዮች ላይ የተሳትፎው ደረጃ ቢለያይም፤ ሕዝብን ማማከርና ፈቃዱን ሰጥቶ እንዲሳተፍ የማድረግ ልምምዶች አሉ፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያውያን ተማክረው ያስቀሯቸው ችግሮች፤ የተሻገሯቸው ፈተናዎች የመኖራቸውን ያህል፤ ባለመነጋገርና መመካከር ምክንያት የከፈሏቸው ከፍ ያሉ ዋጋዎች መኖራቸውን መገንዘቡ ለዚህ አብነት ነው፡፡

ታዲያ እነዚህ መክረው በጋራ የከወኗቸው መልካም ተግባራት በዘመናት ውስጥ ለአብሮነታቸው መሠረት የሆናቸውን ያህል፤ ቁጭ ብለው ሳይመክሩባቸው በግብተኝነት የተፈጸሙ የሚመስሉ ጉዳዮቻቸው ደግሞ ዛሬም ድረስ የዘለቀ ችግር መፍጠራቸው አልቀረም፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ኢትዮጵያውያን የአብሮነታቸውን ያህል በሰላም ማጣት የሚቸገሩት፤ ከግጭትና ጦርነት አዙሪት አልወጣ ያሉት፡፡

ይሄን ችግር ከመሻገር አኳያ እንደ ሀገር ሕዝብ ሊመክር፣ ችግሮችን ነቅሶ ሊፈታ እና ቀጣይ ብዝሃነቱን ጠብቆ የጋራ የሆነች ሀገርን እውን ለማድረግ የሚያስችል ምክክር እንዲያደርግ እድል የሚፈጥርለት ተቋም ተመስርቶለታል፡፡ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በሚል የተቋቋመው ይሄ ተቋም፤ ኢትዮጵያውያን ያለ ልዩነት ቁጭ ብለው በችግሮቻቸው ላይ እንዲመክሩ፣ ቅራኔዎቻቸውን በይቅርታና እርቅ እንዲፈቱ፤ የነገ መንገዳቸውን በጋራ እንዲተልሙ ዕድል የሚፈጥር ነው፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፣ በመንግሥት በኩል እየተካሄዱ ያሉ የሕዝብ ውይይቶች ደግሞ ሌላ የሕዝብን ስሜት ማዳመጫ፤ ችግሮችን በልካቸው አድምጦና ተገንዝቦ ለመፍታት ዕድል የሚሰጥ፤ እንዲሁም ሕዝቡ የመንግሥትን ፍላጎትና መንገድ ተረድቶ አጋዥ ኃይል እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ሚናቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ አበው ችግሩን ማወቅ የመፍትሔው ግማሽ መንገድ ነው እንዲሉ፤ ከሰሞኑ በክልል ደረጃ በተለያዩ ከተሞች፣ በፌዴራል ደረጃም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የተካሄዱ ሕዝባዊ ውይይቶች ዘላቂ ሰላምን እውን ከማድረግ አኳያ የሚኖራቸው አበርክቶ እጅጉን የጎላ ነው፡፡

በተለይ በክልሎች በተለያዩ ከተሞች በከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች (በሚኒስትሮች እና በክልል ፕሬዚዳንቶች ጭምር) እየተመራ ከተካሄደ ሕዝባዊ ውይይት ማግስት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የየክልሎችን እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮችን በጽሕፈት ቤታቸው አቅርበው ማወያየታቸው፤ መንግሥት የሕዝቡን ስሜት ለመረዳት፣ ጥያቄዎቹንም ለማዳመጥ፣ እነዚህ ላይ ተመስርቶም የሚጠበቅበትን የቤት ሥራ ለማከናወን ያለውን ቁርጠኝነት ያሳየበት ነው፡፡

በሕዝባዊ ውይይቶቹ የተነሱ ሃሳቦች በሕዝቡ ውስጥ ያለውን ስሜትና ቅሬታ፣ ጥያቄና መሻት በወጉ ለመገንዘብ ያስቻለ ነው፡፡ ሕዝቡ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱለት፤ የልማት ጥያቄዎቹ እንዲመለሱለት የሚፈልግ ብቻ ሳይሆን፤ አሁን እየታዩ ባሉ ዘርፈ ብዙ ስኬቶች ያለውን በጎ ምልከታ እንዲሁም በቀጣይ የልማቱ ተሳታፊም ተጠቃሚም ለመሆን ያደረበትን ቀና እሳቤ የገለጸበት ጭምር ነው፡፡ መንግሥትም ከሕዝብ የሚጠበቀውን በሚገባ ያስገነዘበበት ነው፡፡

በዚህም ሕዝቡ ሰላሙን አብዝቶ የሚሻ፣ ልማትን የሚናፍቅ፣ የመልካም አስተዳደር ጉዳይን በንቃት የሚከታተል፣ ለዴሞክራሲ መጎልበት የሚታገል... ስለመሆኑ ታይቷል፤ የልማት አጋርነቱንም በልበ ሙሉነት ገልጿል፡፡ ሕዝቡ ይሄን ሲል ደግሞ በመንግሥት በኩል ሰላም የማስፈን ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ፤ የተጀመረውን የልማት መንገድ ማጠናከር እንዲሚያስፈልግ፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ነቅሶ መፍታትና የዴሞክራሲ ባህልን የሚያሳድጉ ጉዳዮች ላይ መሥራት እንደሚጠበቅ የጠቆመበት ነው፡፡

እነዚህ ደግሞ ለመንግሥት ቀጣይ የቤት ሥራዎች የእቅድም የፖሊሲም ግብዓት ጭምር የሚሆኑ፤ ለሰላምና ልማት እውን መሆን ለሚሠራቸው ሥራዎች አዳዲስ ምልከታዎችን የሚጠቁሙ፤ ሕዝቡ ምን ቢደረግለት በምን መልኩ የሰላሙም፣ የልማቱም አቅም መሆን እንደሚችል ያመላከቱ ናቸው፡፡ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ምላሽና ማብራሪያዎች መረዳት የተቻለውም ይሄንኑ ሀቅ ነው፡፡

ይሁን እንጂ አንዱ የቤት ሥራ ሰጪ፣ ሌላው የቤት ሥራ ተቀባይ ሆኖ ከችግር መሻገር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ሕዝብ ጠያቂ ብቻ፣ መንግሥት ተጠያቂና መልስ ሰጪ ብቻ መሆን የለበትም፡፡ የእነዚህ ዓይነት መድረኮች አንዱ ዓላማም ከዚህ ዓይነት እሳቤ መውጣት ነው፡፡ ጠያቂው ጥያቄ እንዳለበት እንዲገነዘብ፤ ተጠያቂውም ጥያቄ እንዳለው እንዲታወቅ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በመድረኮቹ ላይ የነበረውም ይሄው መንፈስ ነው፡፡ ተሳታፊዎች መንግሥትንም ይጠይቃሉ፤ ራሳቸውንም ተጠያቂ ያደርጋሉ፡፡ መንግሥትም ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ፤ ለተሳታፊዎች ደግሞ የቤት ሥራዎቻቸውን ምን ያህል ተገንዝበው እየተወጡ ስለመሆኑ ራሳቸውን እንዲጠይቁ ሲያደርግ ነበር፡፡

በዚህ መልኩ ሁሉም ጠያቂ፣ ሁሉም ተጠያቂ እና ሁሉም የቤት ሥራ ሰጪና ተቀባይ ሆኖ መገለጡ ደግሞ፤ እንደ ሀገር ይሄ ጉዳይ የመንግሥት ብቻ ነው፤ ይሄኛው ደግሞ የሕዝብ ነው የሚል ጣት መጠቋቆም እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ሁሉም በጋራ መክሮ እና ለችግሮቹ የጋራ መፍትሔ እንዲያስቀምጥ፤ ለመፍትሔዎቹም በጋራ እንዲሠራ ዕድል ይፈጥርለታል፡፡ የሰሞኑ ሕዝባዊ መድረኮችም በዚህ መንፈስ ተቃኝተው የተከናወኑ እንደመሆናቸው፤ እንደ ሀገር የሚፈለገው ዘላቂ ሰላም እውን እንዲሆን፣ ልማቱም እንዲፋጠን እና በጥቅሉ ሁሉን አቀፍ ብልጽግናን እውን ለማድረግ ለሚደረገው ጉዞ አቅም ናቸው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በቀጣይ የሴቶችን ቀን ስናከብር ...

**መኩሪያ አስማየሁ**

ዓለማችን እንደየቀለማቸው ብዙ የሚዘከሩ ዕለታት አሏት፡፡ ቅዱሳን ይዘከራሉ፣ ጀግኖች ይወደሳሉ፣ ሊቃውንት ይታወሳሉ፣ ሰማዕታት ይታሰባሉ...፡፡ የነጻነት ቀን፣ የድል ቀን፣ የእናቶች ቀን፣ የአረጋውያን ቀን፣ የላባደሮች ቀን፣ የአርበኞች ቀን፣ የሕፃናት ቀን፣ የሰማዕታት ቀን... ይከበራሉ፤ ይታሰባሉ፤ ይዘከራሉ፡፡

ዛሬ በብዕር ልሳን «ማርች 8» ወይም የሴቶች ቀን መች መከበር ተጀመረ? እንዴት መከበር አለበት... ከመሳሰሉ ሃሳቦች ዘለል ብለን የኢትዮጵያውያን ታዳጊና ወጣት ሴቶች እንደነጮቹ ሴቶች ለአደባባይ አንሰናል ከሚል ስሜት ተነስተው ነው ማክበር ያለባቸው? ወይንስ የቀደሙ ኢትዮጵያውያን ጀግኒቶቻቸውን ክብር ማስመለስና እነርሱን አርአያ ማድረግ ነው ያለባቸው በሚለው ላይ ነው፡፡

በርግጥ በእኛ ሀገር ብሒል «ሴት ለማጀት ወንድ ለችሎት» የሚል ይህንና መሰል ትርጓሜን ያዘሉ ሃሳቦች አሉን፡፡ ይህ ዓይነት አስተሳሰብ እሾህና አሜኬላ ሆኖ ከመንገድ ያላስቀራቸው ዛሬም ቢሆኑ በርካታ እህቶችና እናቶች በየመስኩ ሞልተዋል፡፡ ማርች 8 በዓለም ላይ የሚከበርበት ዐበይት ምክንያት የወል ሰውነትን መሠረት በማድረግ ሰብአዊነት ሳይጣስ፤ ክብረ ሕሊና ሳይነካ፤ ዕውቀት፣ ክህሎትና ጥበብ በፈቀደ መጠን እኩል ሠርቶ ለመግባት ተወዳዳሪና በልክ መኖርን ለማስፈን የታሰበ መልካም ዕይታ ነው፡፡ ይህ የዓለማችን የጋራ ግንዛቤ ሲሆን በተለየ መልክ ግን የሴቶች ቀንን ተመስርቶ የቀደሙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ብቃትንና ማንነትን ማየቱ የተሻለ ነው፡፡

በቅርብ ትናንታችን የአንደኛ ዓለም ሀገራት የሚባሉት እንኳ እንደነርሱ የሰው ልጅ የጋራ ኑረት ጅማሮ አስተሳሰብ፣ ከአደንና ፍሬ ለቀማ ዘመናቸው ጀምረው እስከ 19ኛው ክ/ዘ መባቻ ድረስ በዘር፣ በቀለምና በጾታ ጽንፍ የደረሰ አድሎና ልዩነት ነበራቸው፡፡ በዓለም ላይ ትናንትም ቢሆን እኩልነት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በምልዓት ሲተገበር ኖሯል ማለት አይደለም፡፡ ለዚህም አሜሪካውያን፣ ምዕራባውያን፣ መካከለኛውና ሩቅ ምሥራቃዊያንንም ጨምሮ ከጥንት ጀምሮ ሴቶችን ወደ አደባባይ ያመጡበት ታሪክ አናሳ ነው፡፡

ዛሬ ላይም ቢሆን በእነዚሁ የአደጉ ሀገራት በፖለቲካው፣ በምጣኔ ሀብቱ፣ በወታደራዊ አመራሩ እና በመንግሥት አስተዳደሩ ሥልጣን ላይ ቁንጮ መሆን የወንዶች የበላይነት ሚዛን ይደፋል፡፡ በቀላሉ የዓለማችን ቢሊየነሮች፣ የሀገር መሪዎች፣ ጀነራሎች፣... ወንዶች ናቸው፡፡ ሌላው ቢቀር ጥሩ ዶላር የሚያሳፍሰውን የወጥ ቤትን ሥራ «ሼፍ» የሚል የሙያ ቅፅል ይዘው ገበያውን ተቆጣጥረውታል፡፡ ደመወዝ የሌለውን ልጅ ለማሳደግና ቤት ለመምራት የሚያለፋውን ሥራ «የቤት እመቤት» በሚል ሽፋን ይታለፋል እንጂ ለአደባባይ የበቁ እንኳን ጥቂት እንስቶች ናቸው፡፡

ዓለም ማርች 8ን ሲያከብር የሚያሳምኑ ነገሮች ስላሉት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ግን የሴቶች ቀን ማክበር ነው ወይንስ ለዓለም የሚተርፉ ጀግኒቶችን በመዘከርና አርዓያነታቸውን በመከተል ታላቅነታቸውን መጋራት ነው የሚቀድመው? ድፍን ዓለም ከእያንዳንዱ ሀገር አርዓያ የሚሆኗቸውን ሴቶቻቸውን በጋራ ይዘው ቢመጡ እንኳ ኢትዮጵያ ያላትን ያህል የጎላ ተጽእኖ ፈጣሪ ያላቸው አይመስልም፡፡

ለምሳሌ ያህል አብነት የሚሆኑንን ጥቂቶችን ከምናስታውሳቸው፤ ንግሥት ካሶፒን እናገኛለን፡፡ ይህች ንግሥት የዓለም ሴቶች በከዋክብትና በፕላኔት፣ በፀሐይና በጨረቃ መካከል ያላቸውን መሠረታዊ ልዩነቶች በቅጡ ሳይረዱ ወደሰማይ በማንጋጠጣቸው ብርሃንና ሙቀትን ከመጠቀም ሳይዘሉ፤ እርሷ ግን የከዋክብትን አሰላለፍ ከነሠራዊታቸው ታጠና፣ ትመረምርና ትራቀቅ ነበር፡፡ ለዚህም ብቃቷ ስሟን በታሪክ የወርቅ መዝገብ አስከትባለች፡፡

ሌላዋ ደግሞ ከክርስቶስ ልደት ከ1000 ዓመታት በፊት የዛሬ 3000 ዓመት ላይ በዓለም ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ኢትዮጵያዊት ንግሥት ተከሰተች፡፡ ታላቁ መጽሐፍ ንግሥት አዜብ ይላታል፡፡ ይህች ፈርጥ ታላቋን ኢትዮጵያን ታስተዳድር፣ ትመራ ነበር፡፡ በሀብቷም ወደር የማይገኝላት ነበረች፡፡ ንጉሥ ሰለሞን በዘመኑ ከተቀበለው ስጦታ የንግስተ አዜብን ያህል የሰጠው እንደሌለ በታላቁ መጽሐፍ /በመጽሐፍ ቅዱስ / ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ በዕውቀቷም ቢሆን እንደዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት የንግሥተ አዜብን ያህል ሴት አዋቂ ዓለም አላስገኘችም ብሎ ያምናል፡፡

ምክንያቱም ጠቢቡ ሰለሞን ከርሱም በፊት ሆነ ከርሱም በኋላ እንደርሱ ያለ ጠቢብ አይነሳም ተብሎለታል፡፡ ታዲያ ይህን ከሰው ልጆች በጥበቡ ልዩ የሆነውን ሰው በእንቆቅልሽ ፍልስፍናዋ ልትፈትነው መቻሏ ከርሷም በፊት ከርሷም በኋላ እንደርሷ ያለ ጠቢቡን የምትፈትን ሴት ዓለም አታስገኝም ማለት የሚቻል ሥነ አመክንዮ ይመስላል፡፡ በመልኳም ቢሆን ንጉሡ ሕጋዊ ሚስቶችና ቆነጃጅት ዕቁባቶች በብዙ አኀዝ ቢኖሩትም በውበቷ ልቡን አርዳዋለች፡፡ እንደ እንግዳ ብቻ ተቀብሎ አልሸኛትም በማኅጸኗ ዘር ቋጥሮ ቀዳማዊ ምኒልክን በርሷ በኩል ሰጥቶናል እንጂ፡፡

ልክ እንደ ሁለቱ ፈርጦች እንደ ከዋክብት በደመቁ ሥራዎቻቸው ተጽዕኖ ፈጣሪ እንስት ኢትዮጵያውያን አሉን፡፡ እንደ እቴጌ ሰብለ ወንጌል፣ እንደ እቴጌ ምንትዋብ፣ እንደ እቴጌ ጣይቱ፣ እንደ ባለቅኔዋ ሊቅ እማሆይ የቅኔ ወንበር ዘርግተው ያስተማሩ ፣ እንደ የሙዚቃ ፈርጧ እማሆይ ጽጌ ማርያም እንዲሁም ከአፍሪካ እስከ ሩቅ ምሥራቅ ያሉ ሀገራትን ያስተዳደሩ የንጉሥ እንደራሴ ሕንደኬዎች ሞልተዋታል፡፡

በቅርቡ 100 ዓመታት ውስጥ እንኳን ከተዘመረላቸው እስካልተዘመረላቸው ሀገር ያፈራቻቸው አርበኞች፣ ምሁራን፣ የሳይንስና የኪነ ጥበብ ሰዎቻችን ያሉን ፈርጦች ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡ ሌላው ቢቀር እንደ ኢትዮጵያዊ እናቶቻችን ጀግንነት ልናይ እንችላለን፡፡ ልጅ ያሳደጉበትና መልካም ሰው ለማድረግ የለፉበት ጥበብ፣ ቤት ያስተዳደሩበት ብቃት፣... ዋጋው ስንት ይሆን? የትኛው ጀግንነት ይመልሰውና ይክሰው ይሆን? ይህን ያህል አርዓያነትና ታላቅነት እንዴት ችላ ይባላል? ከዚህ አንጻር የእናት መታሰቢያ ቀኗ ስንት ይሆን?

የሴቶችን ቀን ሌሎች ቢያስቡት ስለፍትሐዊ ዕድልና እኩልነት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ዛሬ ላይ ከጀግኖቻቸው ተናጥበው እንጂ ሴትን ማግነንና ለአደባባይ ማብቃት ለኢትዮጵያውያን አዲስ አይደለም፡፡ ከቀሽም እዬዬ በመላቀቅ የትናንቶቻችንን ሴቶችና ሥራዎቻቸውን ወደፊት ብናመጣና ዛሬም በፈርጦቻችን ላይ ማጌጥ ቢቻል ቀኑን በእጥፍ ማክበር ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን ሴቶች ሀገር የሰሩ፣ ዳር ድንበር የጠበቁ፣ በጥበባቸው ዓለምን ያስደመሙ... እንደሆኑ ታሪክ ዘግቦ አስነብቦናል፡፡

ዛሬ አብዛኛው ወጣት ኢትዮጵያውያን ሴቶች የአርዓያነት መንገድ ምን ይመስላል ቢባል መልሱ ቀላል ነው፡፡ የአሜሪካውያንና የአውሮፓውያን የሲኒማውና የሙዚቃው ኢንዱስትሪ፣ የፋሽንና የስፖርቱ ዓለም ሰዎች ልቦናቸውን ሰልቧቸው ራሳቸውን አብነት የሚሆኑ ጀግኒቶችን አስረስቷቸዋል፡፡ ትኩረታቸውም የነጮቹ የአልባሳት ቅዳቸው፣ የጸጉር ስታይላቸው፣ የፊት ቀለማቸው፣ የቋንቋ ቅላጼያቸው፣ የአረማመድ ቄንጣቸው፣ የአምልኮ ትሩፋታቸው... በአጭሩ የዕለት ተዕለት የኑሮ ዘይቤያቸውን ከፉና ደጉን ሳይለዩ ሾላ በድፍን መከተል ሆኗል፡፡ በዚህ ከብዙ መልካም ሃሳቦችና ጥበባት ከሀገር ልጆች ምሳሌዎቻቸው ተናጥበው ይታያሉ፡፡

ጥንትም ሆነ ዛሬም አብነት የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ግን አሉታዊ ትርጓሜ ያላቸው ብሒሎችና የማኅበረሰብ ሥርዓቶችን ተገዳድረውና አልፈው ለሁሉ የሚተርፍ ሰብእናን ገንዘብ አድርገዋል፡፡ ከዓለም ሴቶች ቀድመው ከወንድ እኩል መሆን ስላሳዩን ወደ ራስ ሰው መመለስና አብነት አድርጎ መኖር መልካም ዕድል ነው፡፡ ዛሬም በተለያዩ ተጽዕኖዎችና በግንዛቤ ማነስ እና በፍትሕ ማጣት ጭምር ሴቶች /እናቶች፣ እህቶችና ሕፃናት/ ላይ የሚያጠይም ድርጊትና ሃሳብን ሁሉም በአንድ እጅ ሊታገል ይገባል፡፡

በይበልጥ ግን የአርዓያነት ድርሻ ያለባችሁ የተለያዩ የሕይወት ተግዳሮቶችን ሰንኮፍ መንግላችሁ የጣላችሁና ሕልማችሁ ላይ የደረሳችሁ በተለያዩ የሙያ መስክ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ያላችሁ ሴቶች ግድ ይላችኋል፡፡ ለዚህም ታዳጊና ወጣት ሴቶችን ከሕይወት ልምዳችሁ፣ ካለፋችሁበት ውጣ ውረድ፣ ከደረሳችሁበት ስኬት ... ልታስተምሯቸውና የሕይወትን መንገድ ልትጠቁሟቸው ይገባል፡፡ ‹ሴትን ማስተማር ቤተሰብን ማስተማር ነው › ይባላልና የሕፃናትን መሪ መንገድ ጠቋሚ ዕውቀት ለጋሽ፣ ተስፋ ሰጪ... የሆኑ እናቶችንና እህቶችን ማፍራት ከምንም በላይ መልካም ሀገርና ዜጋን መገንባት ነው ፡፡ ለእንዲህ አይነት ሕልም በመኖር ማርች 8ን ማሰብ አብዝቶ ማትረፍ ነው፡፡

# የችግሮቻችንም ሆነ የመፍትሔዎቻቸው ባለቤት እኛው ነን!

**ታሪኩ ዘለቀ**

ሕዝብ ማንኛውንም ጥያቄ የመጠየቅ፣ መንግሥትም ከሕዝብ ለሚነሱ ማናቸውንም ጥያቄዎች ጆሮ ሰጥቶ ምላሽ የመስጠት ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ግዴታም አለበት። ሕዝባዊ ውይይቶች የዜጎችን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ዕድል ይጨምራሉ። መንግሥትም የሕዝብ ጥያቄዎችን አድምጦ ፈጣን ምላሽ መስጠት እንዲቻል አስፈላጊነታቸው ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ከሰሞኑ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች የተደረጉና እየተደረጉ ያሉ ሕዝባዊ ውይይቶችም ይህንኑ ታሳቢ ያደረጉ ናቸው። በውይይቶቹም በየአካባቢው ያሉ የመልካም አስተዳደር፣ የልማትና ሌሎችም ጥያቄዎች ተነስተው ሰፊ ውይይቶች ተደርገውባቸዋል። ከውይይቶቹም ዜጎች ብዙ እንደሚጠብቁ ይታመናል።

ሕዝባዊ ውይይቶቹ ከጥያቄ ባለፈ ፍሬ እንዲኖራቸው በየአካባቢው ያሉ አመራሮች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። በከፍተኛ አመራሮች ደረጃ የተነሱና ምላሽ የተሰጠባቸው፣ ለመፍትሔያቸው ቃል የተገባላቸው ጥያቄዎች ወደ ተግባር እንዲቀየሩ በቀጥታ ከሕዝብ ጋር የሚገናኙት የወረዳና የቀበሌ አመራሮች የተቀናጀ አሠራር መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ በየአካባቢው ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ተረድቶ ሕዝብን በአግባቡ የሚመራ፣ ችግሮችን የሚፈታ ብቁ አመራር ማስቀመጥ አስፈላጊና ግዴታም ነው። ሁሉም ውጤት በመንግሥት ሥራ ብቻ የሚመጣ ባለመሆኑም ኅብረተሰቡ ከአመራሩ ጎን በመሆን ለተግባራዊነቱ በመትጋት ማገዝ ይገባዋል።

ከዚህ ባለፈ ችግሮች በአንዴ ንግግርና ውይይት ብቻ የሚፈቱ ባለመሆናቸው መሰል ሕዝባዊ ውይይቶች በተከታታይ ሊደረጉ፣ ሕዝቡ ከአመራሮች ጋር የሚገናኙበት ሃሳባቸውን በነፃነት የሚገልፁበት መድረኮች ቀጣይነት ሊኖራቸው ይገባል።

ሕዝባዊ ውይይቶቹ ሕዝቡ ጠያቂ ብቻ ሳይሆን የመፍትሔ አካል እንዲሆን የተሻለ ግንዛቤ ለመፍጠር እንደሚያስችሉ ይታመናል። ወካይ ከሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር መወያየት ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣትም ትልቅ አቅም ነው።

ሀገራችንን በልማት ወደ ብልጽግና ለማሻገር ቅድሚያ ለሰላም ሰጥተን መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል። ይህንን እውን ለማድረግ በችግሮቻችን ዙሪያ በግልጽ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ እና ወሳኝ ነው።

ከዚህ አንጻር፣ ሕዝብን እና አመራሩን ፊት ለፊት ያገናኙ ሕዝባዊ ውይይቶች ከሰሞኑ መደረጋቸው ጠቀሜታቸው ከፍ ያለ ነው። በእነዚህ ውይይቶች ዜጎች በሕይወታቸው ፈተና የሆኑባቸውን ነገሮች በቅሬታ ከተሞሉ መዝገቦቻቸው አውጥተው ለመድረክ አቅርበዋል። ከእነዚህ የሕዝብ ቅሬታዎችና ጥያቄዎች መካከል የሰላም እጦት፣ የኑሮ ውድነት፣ የመሠረተ ልማት ችግርና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ገዝፈው ታይተዋል።

በርግጥ ውይይቶች ለዓመታት ሰሚ ላጡ ዜጎች ጆሮ የሚያውሱ ናቸው። መሰል ልምምዶች በሕዝብና በመንግሥት መካከል መግባባትን የሚፈጥሩ ናቸው። ፋይዳቸውም ላቅ ያለ ነው። መንግሥት የሠራቸውን፣ የሚሠራቸውን ለሕዝብ በአግባቡ ለማስረዳት እና ለማስገንዘብ ዕድል የሚሰጡ ናቸው።

በአለንበት ዘመን በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚፈበረኩ መሠረተ ቢስ መረጃዎችን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጥሩትን ግራ መጋባት በትክክለኛ መረጃ ለማረምም ሕዝባዊ ውይይቶች የሚፈጥሩት መልካም አጋጣሚ ትልቅ እንደሆነ ይታመናል። ዘላቂ ሰላምን በውይይት ለማስፈን የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው።

ሰላም ከሌለ ነገ የለም። ስለ ነገ ማሰብም ማቀድም የሚቻለው በሰላም ውስጥ ብቻ ነው። በሀገሪቱ ባለፉት ጊዜያት ይህ ለሁሉ ነገር አስፈላጊ የሆነው ሰላም ጥላ እያጠላበት መጥቷል። በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ሕዝቦች ሰላምና መረጋጋት እርቋቸው ታይተዋል። የእርስ በእርስ ግጭት በርካቶችን ወደ ችግር እንዲገቡ ምክንያትም ሆኗል። ይህ ደግሞ ሀገሪቱንና ሕዝቦቿን ያልተገባ ዋጋ አስከፍሏል።

ውስን በሆነው የምድር ቆይታችን ለፀብ የሚሆን የሚተርፍ ጊዜ እንደሌለን በመገንዘብ ፍቅርና

> **በ**ርግጥ የሃይማኖት ተቋማት ተገቢውን ትምህርት ለተከታዮቻቸው ማስተማር ሃይማኖታዊ ግዴታቸው ቢሆንም ያንን ማድረግ በቻሉ ልክ ግን ሰላምን በሀገሪቱ ማስፈን ይቻላል

መተሳሰብን ባህል ለማድረግ ቁጭ ብሎ መወያየት ትርፉ ብዙ ነው። መልካም ዕሴቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸሩ መምጣታቸው፣ ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ለማፅናት ፍላጎት ማጣታችን፣ ባልተገቡ ምክንያቶች በሚነሱ ግጭቶች ሳቢያ በርካቶች በሕይወት መኖርን እየሻቱ ላይመለሱ አሸልበዋል።

ሰላም የሁሉም ነገር መሠረት መሆኑን በመረዳት እንዲሁም የሰላም ዋጋ ምን ያህል ውድ እና የማይተካ እንደሆነ ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል። የእያንዳንዳችን ሰላም እንዲጠበቅ የጎረቤታችንን ሰላም መጠበቅ አለብን። የሰላም ዋጋ ከገባን የእኛ ሰላም እንዲጠበቅ በእኛ ምክንያት የሌሎች ሰላም እንዳይታወክ መጠበቅ፣ ሰላማቸውን እንደ ራሳችን ሰላም አድርገን እየቆጠርን በጥንቃቄ መጠበቅ ከቻልን ምድራችን የሰላም መዲና ትሆናለች። መንደሩም፣ ቀዬውም፣ ከተማውም፣ ሀገሩም ሰላም ይሆናል።

በሰላም መደፍረስ ምክንያት ለሚከሰቱ ችግሮች ቀዳሚ ሰለባ የሚሆኑት አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት ሕፃናት፣ ሴቶችና አቅመ ደካሞች መሆናቸው ሲታሰብ የሰላም ዋጋ ምን ያህል ውድና የማይተካ መሆኑ እሙን ነው። ስለ ሰላም የሚሰብኩ የሃይማኖት አባቶች፣ የመንግሥት ተወካዮች አልያም ግለሰቦች በቅድሚያ ራሳቸው ኖረውት ምሳሌ ሆነው መገኘት አለባቸው።

ዛሬም ከተጣበቀን የኋሊት ጉዞና ከድህነት ቀንበር መላቀቅ የምንችለው ሰላማችንን ስንጠብቅ ብቻ ነው። በርካታ ቁጥር ያለው ኢትዮጵያዊ አነሰም በዛም በሚከተለው ሃይማኖት ስለ ሰላም ይነገረዋል። ያንን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ አለበት። የሀገራችን ሰላም እንዲጠበቅ፣ በሀገሪቱ ሰርተን እንድንለወጥ የሰላም አስፈላጊነትን በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል።

ወቅቱ በጾምና ጸሎት ወደ ፈጣሪ የምንቀርብበት ጊዜ ነው፤ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ለሀገራችን ሰላም አብዝተን የምንጸልይበት ሊሆን ይገባል። በሰላም ጉዳይ ሰፊ ጊዜ ወስደው የሃይማኖት አባቶች ምዕመኖቻቸውን ሊመክሩ ሊያስተምሩ ይገባል።

በርግጥ የሃይማኖት ተቋማት ተገቢውን ትምህርት ለተከታዮቻቸው ማስተማር ሃይማኖታዊ ግዴታቸው ቢሆንም ያንን ማድረግ በቻሉ ልክ ግን ሰላምን በሀገሪቱ ማስፈን ይቻላል። በሰላም ጉዳይ ላይ የእምነት ቤቶች ልዩ ትኩረት ሰጥተው ማስተማራቸው፣ ሕዝቡን ማሰልጠናቸው ደግሞ ሀገራዊ ጠቀሜታው ግዙፍ ነው።

ከየትኛውም ምድራዊ ተቋም በበለጠ የሃይማኖት ተቋማት ስለ ሰላም፣ አብሮ ስለመኖር፣ የሌላውን ሕይወት እንደራስ አድርጎ ስለማክበር፣ ባልንጀራን ስለመውደድ እና ሌሎች ወርቅ የሆኑ አስተምህሮቶችን ማስተማር የየዕለት ሥራቸው ሊሆን ይገባል።

ሰላም ዋጋ የማይተመንለት የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው። አሁን እየታየ ያለውን መልከ ብዙ የግጭት ጠማቂን በመለየት፣ የሰላም መደፍረስ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ጉዞ እንቅፋት መሆኑን በመረዳት፣ በጦርነትና በብጥብጥ የሚፈታ ችግር አለመኖሩን በማወቅ ግልፅ ውይይት ማድረግ ተገቢ ነው።

ከዚህ አንጻር የመንግሥትና የሕዝብ መወያየትና መደማመጥ ለመልከ ብዙ ችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ ለማፈላለግ ወሳኝ መሆኑ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም። ለተሻለ ሰላም ሕዝብና መንግሥት ተደማምጠው መጓዝ ይጠበቅባቸዋል። በቀጣይ ተግባራዊ የሚደረገው ብሔራዊ ምክክርም የዚሁ እውነታ አንድ አካል ነው። የቆዩ ችግሮችንና ቁርሾዎችን ለመፍታት ከመጣር ጀምሮ እንዲህ እንደ አሁኑ ከሕዝብ ጋር መወያየት እጅግ ጠቃሚ የሚያቀራርብ፣ የሚያስተዋውቅ፣ ችግሮችንም ለመረዳትና ለመፍታት የሚያገለግል ነው።

መንግሥት አሁን ላይ ከሕዝቡ ጋር እያካሄደ ያለው የፊት ለፊት ውይይት ችግሮቻችንን በመነጋገር ለመፍታት ትልቅ አቅም ቢሆንም፣ ከዚህ ጎን ለጎን በእየለቱ የሕዝብን ድምፅ መስማት የሚቻልባቸውን መንገዶች ማመቻቸት ተገቢ ነው። የድሮ መንግሥታት ‹‹እረኛ ምን አለ›› ይሉ እንደነበረ ሁሉ የአሁን መንግሥታትም ‹‹ሚዲያው ምን አለ›› የሚል እለታዊ ምልከታና ግምገማ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ ደግሞ ለሕዝብ ጥያቄ መልስ መስጠት የማይፈልግ የሥራ ኃላፊንም ለምን ብሎ ለመጠየቅ ያስችላል።

ሰሞኑን በተደረጉ ሀገር አቀፍ ውይይቶች የሕዝብ ድምጾች ተሰምተዋል። መንግሥትም የሚወስደውን ወስዶ የግንዛቤ ችግሮችንም ግልፅ አድርጓል። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ማንሳት ተገቢ ነው። የመጀመሪያው ተግባራዊ ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን ወዲያውኑ መመለስ ሲሆን ሁለተኛው እና ዋነኛው ደግሞ እኛስ እንደ ሕዝብ ምን ማድረግ ይገባናል? ብሎ ለተግባር መነሳት ነው።

አሁን ወቅታዊ የሆኑ የሰላም፣ የኑሮና መሰል ችግሮቻችን እኛው ውስጥ ያሉ/ የውጭ ጠላቶቻችን ባልተገባ መልኩ አራግበዋቸው ይሆናል እንጂ/ ምንጮቹ እኛው የሆንባቸው ናቸው። መነሻው እኛው ከሆንን መፍትሔም እኛው ነን። መፍትሔ ማምጣት ግን ትንሽ ጥረትን፣ ትንሽ ትጋትን ብሎም መስዋዕትነትን ይፈልጋል።

ሌባ ሌላ ሰውን ሲሰርቅ ‹‹ነገ በእኔ ነው›› ብሎ ዛሬ ላይ ከማጋለጥ፣ ሙሰኛና ዘረኛ ባለሥልጣን ሲያጋጥም እስከ መጨረሻው መብትን ለማስከበር ከመታገል ይጀምራል። የውሸት፣ አፍራሽና የጥላቻ የማህበራዊ ሚዲያንም ከማውገዝ እና የሚረጩትን መረጃ ካለማባዛት ይጀምራል። እነዚህንና መሰል ነገሮችን ማድረግ ከጀመርን ነገ ታላቅ ታሪክ መሥራት እንችላለን።

በቅርቡ ሀገራችንን ከመፍረስ ያዳነው እኛው ነን። ትልቁን ነገር ችለን እንዴት ትንሹ ያሸንፈናል? ርግጥ ነው ለሁሉም ነገር ጀማሪ፣ መሪ ያስፈልገዋልና መንግሥት የመጀመሩን ኃላፊነት ወስዷል፤ እኛ ደግሞ እንከተል፤ ያኔ ሀገራችን በሁሉ ነገር ትቀድማለች፡፤

ከኢትዮጵያዊነት ወግና ባህል ያፈነገጡ ጉዳዮችን ሰከን ብሎ ማየት ያስፈልጋል። ሰላም በዋጋ አይተመንም። ሰላም ከምንተነፍሰው አየር ያልተናነሰ ዋጋ አለውና ሁሉም ሰላሙን ይጠብቅ።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ሰው ሠራሽ አስተውሎት- ለዲፕሎማሲው ዘርፍ ያለው ሚናና ተፅዕኖ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በየጊዜው እየረቀቀ የመጣው ሰው ሠራሽ አስተውሎት (Artificial intelligence) ለሰው ልጅ ዕድል ብቻ ሳይሆን ስጋት ይዞ መምጣቱ ይነገራል። በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሰው ሠራሽ አስተውሎት አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ "የሰው ልጅ ከፈጠረው ሁሉ እጅግ ጠቃሚው፣ እጅግ አደገኛው ሰው ሠራሽ አስተውሎት ነው" ሲሉ መናገራቸው ይታወሳል። ይህም የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ እያደር መምጠቅ ዕድልን ብቻ ሳይሆን ስጋትንም ፤ ሁለቱንም በአንድ ላይ ይዞ የሚመጣ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

አሁን ላይ ግን የሰው ሠራሽ አስተውሎት በዓለም ወደ ረቀቀ ደረጃ እየደረሰ የበለጸጉት ሀገራት የተጠቀሙበትና የኢኮኖሚያቸው እድገት መሠረት እያደረጉ ይገኛሉ። መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ የሰው ሠራሽ አስተውሎት የዓለም ኢኮኖሚ በስፋት እያንቀሳቀሰ ነው። እ.ኤ.አ 2022 ሦስት ነጥብ አንድ ትሪሊዮን ዶላር ሀብት ያንቀሳቀሰ ሲሆን፤ እስከ እ.ኤ.አ በ2030 ለዓለም ኢኮኖሚ 15ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ሀብት ሊያንቀሳቅስ ይችላል ተብሎ ተገምቷል።

በዚህ ልክ የዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣ ተፅዕኖ እያሳደረ ያለው ሰው ሠራሽ አስተውሎት የዓለም ኃያላን ሀገራት የሚባሉት ሳይቀር ፉክክር ውስጥ እየከተተ መሆኑ ይነገራል። ይህ ደግሞ በተለይ በቴክኖሎጂ የዳበረ ልምድ በሌላቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገራት ላይ እያስከተለ ያለው ተፅዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም። ታዲያ እነዚህ ሀገራት ተፅዕኖም በመከላከል ቴክኖሎጂው በመጠቀም ረገድና መሥራት ያለባቸው ብዙ የቤት ሥራዎች እንዳሉም የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

በኢትዮጵያ መንግሥት የሰው ሠራሽ አስተውሎት በኢንስቲትዩት ደረጃ እንዲቋቋም በማድረግ ትኩረት ሰጥቶ በርካታ ሥራዎች እየሠራ ይገኛል። በተለይ የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ሀገሪቱ ተጠቃሚ ሆና ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንድትደርስና በሁሉም ዘርፎች ተጠቃሚ መሆን እንድትችል መደላድል የሚሆኑ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

በቅርቡም ዓለም አቀፋዊ የሰው ሠራሽ አስተውሎት አስተዳደር ሥርዓት ጅምሮች እና የኢትዮጵያ ትልም ላይ ያተኮረ ምክክር በአዲስ አበባ ተካሂዷል። ምክክሩ የሰው ሠራሽ አስተውሎት በውጭ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲ ተልዕኮ ላይ ያለውን ጠቀሜታ እና ተጽዕኖ ለማስገንዘብ ያለመ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጃፋር በድሩ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ዓለም በሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርተፊሻል ኢንተለጀንሲ) ወደ ረቀቀ ደረጃ ላይ ደርሳለች። የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ጥቅሞች የማይተኩ ናቸው። ሆኖም ግን ሀገራችን በቴክኖሎጂ ከአፍሪካ ሀገራት ግንባር ቀደም ተጠቃሚ መሆን የምትችልበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰች ሀገር አይደለችም። በመሆኑም አሁን ላይ ዓለማችን ብሎም የሀገራችን ወሳኝ አጀንዳ የሆነው የሰው ሠራሽ አስተውሎት ምክክር አስፈላጊ ነው።

‹‹የሰው ሠራሽ አስተውሎት በዓለማችን ብሎም በሀገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሥርዓት ውስጥ ወሳኝ ነው›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የቴክኖሎጂው ተፅዕኖ በተለያዩ ኢንዱስትሪዎችና ዘርፎች ላይ በሰፊው እየተስተዋለ ይገኛል። በጤና፣ በፋይናንስ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ እና በሁሉም ዘርፎች ላይ መሻሻሎችን የሚያመጡና የኑሮ ሁኔታን ለማቅለል እየመጣ ያለ ወሳኝ ቴክኖሎጂ ነው።

ሰው ሠራሽ አስተውሎት በሁሉም ዘርፍ አበርክቶ እንዳለው ሁሉ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለውም የተለያዩ ጥናቶች ያመላክታሉ። ያደጉት ሀገራት በሰው ሠራሽ አስተውሎት በመታገዝ የጤና፣ የትምህርት፣ የትራንስፖርት፣ የፋይናንስና ሌሎች የሥራ ዘርፎች ማዘመን እና ውጤታማ ማድረግ መቻላቸው በበርካታ ጥናቶች ያሳያሉ ይላሉ።

እንደዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት አድርጎ የፖሊሲና ጥናት የሚካሄድና የዲፕሎማሲ ስልጠና የሚሰጥ ተቋም እንደመሆኑ ፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ከፍተኛ ሚና እና ተፅዕኖ እንዳለው ይረዳል። ቴክኖሎጂውን በወቅቱ ተረድቶ ጠቀሜታውን በማጉላት አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል ከወዲሁ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል። ቴክኖሎጂው አዲስ እንደመሆኑ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰው ሠራሽ አስተውሎት አስተዳደር ማዕቀፎች፣ ትብብሮችና ስምምነቶች ላይ በንቃት መሳተፍ ያስፈልጋል።

ምክክሩ የሰው ሠራሽ አስተውሎት በውጭ ግንኙነትና በዲፕሎማሲያዊ ሊኖረው የሚገባ ሚና እና ተፅዕኖ በፍጥነት በመረዳት በዲፕሎማሲው ዘርፍ የሀገር ብሔራዊ ጥቅም ማስከበር እንዲቻል ከዘርፉ ምሁራን ጋር በመመካከር የመፍትሔ ሃሳቦችን በማመንጨት ያስችላል ተብሎ የታመነበት መሆኑን ነው ዋና ዳይሬክተሩ ያመላከቱት።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን በበኩላቸው፤ ‹‹የሰው ሠራሽ አስተውሎት በተለያዩ ዘርፎች የዓለምን አሰላለፍ እየቀየረ ነው። ቴክኖሎጂው በዓለም አቀፍ በጂኦ ፖለቲካዊ ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ የደህንነት ሥርዓቶች አጋዥም ተግዳሮት ፈጣሪም እየሆነ መጥቷል›› ይላሉ።

‹‹ሀገራችን ይህን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በምታደርገው ጥረት አጋዥ እንዲሆን በዚህ መልኩ ግንዛቤዎች ማስፋት ይጠበቃል›› ያሉት አምባሳደር እሸቴ፤ ቴክኖሎጂ ከጊዜ ወደጊዜ በሀገራት መካከል ያለውን የኃይል አሰላለፍ ጭምር አዲስ ገጽታ እንዲኖረው እያደረገ ነው። ቴክኖሎጂው በዓለም መድረኮች በወታደራዊ አቅሞች ተፅዕኖ በማሳደር የአስተዳደራዊ ሥርዓትን በመቀየር ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በሰው ሠራሽ አስተውሎት ፈጠራ እንዲሁም ሌሎች ልዩ ገጽታን የሚያሳዩ ነገሮች እየመጡ እንደሆነ ያመላክታሉ። ይህም ቀደም ካሉት የቴክኖሎጂ አብዮቶች በጣም የረቀቀ በመሆኑ የሀገራት የበላይነትና የበታችነት በመፈጠሩ ፉክክር ውስጥ ማስገባቱ አይቀሬ መሆኑን አንስተው፤ አሁን ላይ በዚህ የተነሳም ድርድሮች ሳይቀር መካሄድ የተጀመረበት ሁኔታ መኖሩ ለዲፕሎማሲው ተጨባጭ ተግዳሮት እየሆነ መምጣቱ ማሳያ መሆኑን ያስረዳሉ።

‹‹እንደዚህ ዓይነት በሰው ሠራሽ አስተውሎት የሚካሄዱ ውይይቶችን በማስፋት ጠቃሚ ግብዓቶች ለማግኘት ያስችላል። በተለይም በአፍሪካ አህጉር እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት የመሪነቱም ሚና ለመጫወት እንዲችሉ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል እጅግ ጠቃሚ ነው›› ያሉት አምባሳደር እሸቴ ፤ የሰው ሠራሽ አስተውሎት መስፋፋት ከዓለም አቀፍ የደህንነት ሲስተም አንጻር ታይቶ የማያውቅ ፈተና እንደሚያመጣ እየተተነበየ ነው፤ አንዳንድ ምልክቶችም አሉ፤ ከዚህ በላቀ ሁኔታ በሰው ሠራሽ አስተውሎት የሚመሩት ቴክኖሎጂዎች ወሳኝ ዘርፎች ወደሆኑ (የመሠረተ ልማቶች፣ መከላከያ፣ የደህንነት …) ሥርዓቶች እየገቡ የሳይበር ጥቃቶች እና የተሳሳቱ መረጃዎች እየደረሱ መሆኑ በጣም ስትራቴጂክ እየሆነ ይመጣል ማለት ነው። በተጨማሪም ቴክኖሎጂው የኢኮኖሚ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው›› ይላሉ

እንደ አምባሳደር እሸቴ ማብራሪያ፤ በሰው ሠራሽ አስተውሎት ረገድ ያለው ድርድር በውጭ ግንኙነትና በደህንነት ጉዳዮች ሚና በውሉ ተረድቶ የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር እንዲቻል የተጀመሩ ሥራዎችን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ አጠናክሮ መቀጠል አለበት። በተለይ አጀንዳ ቀረጻ ላይ የሚሠራው ሥራ ለሁለት ከፍሎ ማየት ይገባል። የመጀመሪያው በቴክኖሎጂው ትግበራ ሂደት ሀገራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ የሚያስችል አቋም መያዝ ሲሆን፤ ሁለተኛው እንደ ሀገር ዓለም አቀፍዊ የማስተዳደር መንገዶችን ተቋማትን በማደራጀት ዝግጅት በማድረግ አቋም በመያዝ አካሄዶችን ማሳደግና ማዳበር ያስፈልጋል።

"ሀገራችንን ልታገኝ የምትችለውን ጥቅም እንዳናጣ ተወዳዳሪ ሆኖ በመገኘት ቴክኖሎጂውን መከታተልና የተጀመሩ ሥራዎችን ማሳደግ በርካታ ሥራዎችን መሥራት ይገባል" ያሉት አምባሳደር እሸቴ፤ ይህ ሲሆን በቴክኖሎጂው ተጠቃሚ በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘትና የድርሻን ለመቋደስ የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል። እንደዚህ ዓይነት ምክክሮች መደረጋቸውም ጠቃሚ ሃሳቦች የሚንሸራሸሩበት እና ለፖሊሲ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦች የሚፈልቅባቸው መሆናቸውን ይገልጻሉ።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሹሩን ዓለማየሁ (ዶ/ር) ‹‹የሰው ሠራሽ አስተውሎት ያለውን ግዙፍ አቅም ስንመረምር በማህበረሳባችን የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ያለውን በቀጣይ ሊፈጠር የሚችለው ተፅዕኖ ስናይ እንደዚህ ዓይነት ምክክሮች ለሀገር ወሳኝ ጉዳይ ነው›› ይላሉ

‹‹ሀገራዊ ፍላጎቶታችንን ለማሳካት ሰው ሠራሽ አስተውሎት ኃይለኛ መሳሪያ የሆነበት አዲስ ዘመን ላይ ደርሰናል›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህ እውን ይሆን ዘንድ እንደ ሀገር ከሦስት ዓመት በፊት ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ መደረጉን ገልጸዋል። ስትራቴጂው በተለይ በዲጂታል ዘርፍ ኢትዮጵያ ወደ ዲጂታል ማዕከል ለመቀየር ያለመና ኢትዮጵያ ከዲጂታል ኢኮኖሚ የምትጠቀምበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የተዘጋጀ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፤ ስትራቴጂው የዲጂታል መሠረቶችን በመገንባት ረገድ ከፍተኛ ውጤት አምጥቷል። በተለይም የቴሌኮም መሠረተ ልማት በማስፋፋት ብዙ ኢትዮጵያውያን የዲጂታል ዓለም እንዲቀላቀሉ እና የዲጂታል ሥነ ምህዳር እንዲዳብር አድርጓል። ሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች የዲጂታል መታወቂያ እንዲመዘገቡ አስችሏል። በቀጣይ በአጭር ዓመታት ከ90ሚሊዮን በላይ ዜጎች የዲጂታል መታወቂያ እንዲኖራቸው እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ተጠናቅቀዋል። የዲጂታል ቀልጣፋ የክፍያ ሥርዓት እንዲኖርና ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸው፣ በርካታ ሀገራዊ የኢኮሜርስ ፕላትፎርሞች ከመልማታቸውም በላይ እነዚህን ፕላትፎርሞች ተጠቅመው ወደ ሥራ የሚገቡ ቢዝነሶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፣ በርካታ የመንግሥት ተቋማትም አገልግሎታቸውን ወደ ኤሌክትሮኒክ ዘዴ እየቀየሩ መሆናቸው እና የዲጂታል ትራንዛክሽኖችን ለማቀላጠፍ በርካታ አስቻይ የሕግ ሥርዓቶች እንዲኖሩ መደረጋቸው ዋና ዋና ስኬቶች ናቸው ብለዋል።

እነዚህ ስኬቶች የተገኙት የመንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ እና የሁሉም ዜጎች የጋራ ጥረት ማሳያዎች መሆናቸው ይገልጻሉ። ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን የበለጠ ለማሳደግ እና ለማፋጠን የሰው ሠራሽ አስተውሎት እንደ ካታሊስት ሆኖ የማይተካ ሚና ይጫወታል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የሰው ሠራሽ አስተውሎት እድገት ለማፋጠንና የሀገር ተግዳሮቶች ለመፍታት ኃይለኛ መሳሪያን ሆኖ ይቀርባል ብለው እንደሚያምኑም ተናግረዋል።

በሰው ሠራሽ አስተውሎት የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች መሥራት እንደሚቻል ጠቅሰው። ለአብነት፤ በግብርናውን ምርታማነት የሚጨመሩ፣ የጤና ተደራሽነት የሚያሻሽሉ፣ ትምህርትን የሚያሳድጉ በሰው ሠራሽ አስተውሎት የተደገፉ በማህበረሰቡ ፍላጎትን ጋር የሚስማሙ መፍትሔዎች መምጣታቸው፤ የመሠረተ ልማት የሀብት አጠቃቀምን የሚያሻሽሉ መተግበሪያዎች (አፕሊኬሽኖች)መምጣታቸው ለዜጎቻችንን ቀልጣፋና ግላዊ ፍላጎቶቻቸውን መሠረት አድርገው ድጋፍ የሚያደርጉ መሆኑን አስረድተዋል።

‹‹የሰው ሠራሽ አስተውሎት ጥቅም ላይ ማዋል በማስተዋልና በጥንቃቄ መያዝ ይገባል›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርም በሀገሪቱ ኃላፊነት የተሞላበትና የሕዝብ ጥቅምን የሚያረጋግጥ የሰው ሠራሽ አስተውሎት አጠቃቀም እንዲያድግ ድጋፍ ለማድረግ የበኩሉን እየሠራ ይገኛል። በተለይ ከአካዳሚ ተቋማት፣ ከግል ኩባንያዎች ጋር በመተባባር በዘርፉ የምርምርና የልማት ሥራዎችን መደገፍ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ወጣቶች በሰው ሠራሽ አስተውሎት የተደገፉ መፍትሔዎችን በማበጀት የሚያስችል አቅም እንዲገነቡ ማስቻል በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል።

ፈጠራን በሚያበረታታ ጠንካራ የሕግና ቁጥጥር ማዕቀፍ እንዲኖርና ባለድርሻዎች መካከል ትስስር በመፍጠር ጠንካራ የሥነ ምህዳር እንዲፈጠር የበኩሉን እየተወጣ መሆኑን ያመላክታሉ። በተጨማሪ ቴክኖሎጂን ለልማት ለማዋል በሚያደረጉ እንቅስቃሴዎች ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በትብብር ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ አንጻር ከቴክኖሎጂ ልማት ጎን ለጎን የቴክኖሎጂ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎችን የመቅረጽ ሥራዎችን እየተሠሩ መሆኑን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ እንደዚህ ዓይነት በቴክኖሎጂ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ውይይት በሚካሄድባቸው መድረኮች በኢትዮጵያ የተስተካከለ የተቀናጀ እና የቴክኖሎጂ እድገት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ወደፊትም መጻኢ የቴክኖሎጂ ዕድሎች መሰል ውይይቶች የሚካሄድ መሆኑን አስታወቀዋል። ስለዚህ የሰው ሠራሽ አስተውሎትና ሌሎች መጻኢ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ኢትዮጵያ ብልጽግናና እድገት ለማምጣት በጋራ እንሥራ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

> **‹የሰው ሠራሽ አስተውሎት በተለያዩ ዘርፎች የዓለምን አሰላለፍ እየቀየረ ነው። ቴክኖሎጂው በዓለም አቀፍ በጂኦ ፖለቲካዊ ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ የደህንነት ሥርዓቶች አጋዥም ተግዳሮት ፈጣሪም እየሆነ መጥቷል››**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ለኢትዮጵያውያኑ የተበረከተ - የሕዳሴ ግድቡ እውቅና

**አስቴር ኤልያስ**

የኢትዮጵያውያኑ ሁሉ የኩራት ምንጭ በሆነው በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ፣ ኢትዮጵያና ዜጎቿ በተደጋጋሚ ተፈትነውበታል። ይሁንና ፈተናው ይበልጥ ጥንካሬ ፈጠረላቸው እንጂ አንዳችም ጊዜ ቢሆን በፈተናው ተሰናክለው አልወደቁም።

በሕዳሴ ግድቡ ዙሪያ ለሚደርሰው ተደጋጋሚ ፈተና ትልቁን ድርሻ የምትይዘው አፍሪካዊቷ ሀገር ግብጽ ስትሆን፤ ዓይነተ ብዙ የሆኑ ፈተናዎችን በመፈብረክ ከጅማሬው እስካሁኑ ሰዓት ድረስ የተቻላትን ሁሉ አድርጋለች። በርግጥ የግብጽ ስጋት የጀመረው፤ ዛሬ አይደለም። በፊትም ቢሆን የዓባይ ወንዝ ጉዳይ ሲያባንናት የኖረ ነገር ነው። ‘ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ትገነባ ይሆን?’ የሚል ስጋት ሲያባንናት ኖሯል።

ኢትዮጵያ የሕዳሴውን ግድብ ለመገደብ በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትሯ አማካይነት የመሠረተ ድንጋይ ባስቀመጠችበት ወቅት ጥርጣሬዋ እውን ሆኖ ስጋቷ ከፍ ብሎ ግራ ተጋብታ ከርማለች። ስጋቷን በውይይትና በሰጥቶ መቀበል መርህ መቅረፍ ሲገባት ያልተገባ መንገድን መረጠች። በማስፈራራት፣ አንዱን ብሔር ከሌላኛው ጋር በማጋጨትም በሌላ ሌላ ተንኮል አልሆን ሲላት ከአንደኛ አህጉር ወደ ሌላኛው አህጉር ‘ጉዳዬን እዩልኝ ስትል’ ተንከራትታለች። በዚህ መልኩ የግድቡን ግንባታ ለማስቆም ያደረገችው ውጣ ውረድ ሁሉ ከንቱ ድካም መሆኑን የተረዳችው ይህች ሀገር፣ ‘ግድቡ የሚይዘው የውሃ መጠንና ከፍታው ካልተቀነሰ ሞቼ እገኛለሁ’ ስትል ሞገተች።

ነገር ግን ይህ በ2003 ዓ.ም ጅማሬውን ያደረገውና ኢትዮጵያውያኑ እንደ ዓይናቸው ብሌን የሚሳሱለት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ አንድ ሺ 800 ሜትር ስፋት ያለው፣ 145 ሜትር ከፍታ ያለው እንዲሁም 74 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ውሃ የያዘ እና በኢጣሊያኑ ኩባንያ ሳሊኒ ተገንብቶ ወደመጠናቀቅ የተቃረበ መሆን ችሏል።

ከአፍሪካ የአንደኝነትን ደረጃ የያዘው ይህ ግድብ፣ ከዓለም ስምንተኛ ደረጃ ላይ ሲሆን፣ በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ስም ከፍ እንዲል ያደረገ ነው፤ ከዚህ አኳያ ከሰሞኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የስኬት ሽልማት ካበረከቱላቸው ተቋማት መካከል አንዱ መሆን ችሏል። ይህ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በሰባት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ መግለጻቸው የሚታወቅ ሲሆን፣ በዓባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው ድልድይና የፕሮጀክቱ ሙሉ ሥራ በቀጣይ ዓመት የሚጠናቀቅ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የተሰጠውን የእውቅና ሽልማት በማስመልከት ምሁራንን ባነጋገርናቸው ወቅት እንዳሉት ከሆነ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ማለት ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ክብሯ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ በቀጣናው ያላትን ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አቅሟን የሚወስን ታሪካዊ ክስተት ነው። እውቅናው ለኢትዮጵያውን የተሰጠ ነው።

በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪ ሰማኸኝ ጋሻው እንደሚሉት ለአምስቱ መሥሪያ ቤቶች ሽልማት የመሰጠቱ ፋይዳ ላቅ ያለ ነው። ተቋማቱ በሀገር ደረጃ ሲታዩ የአንድ ሀገረ መንግሥት ህልውና መሠረቶች ናቸው። የመንግሥቱን ቀጣይነትም የሚወስኑ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ናቸው። በተጨማሪም ከሰፊው ሕዝብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው የአገልግሎት ማዕከላት ናቸው። መንግሥት ለኅብረተሰቡ የሚሰጠው ሁለንተናዊ አገልግሎት ውጤታማነትና ድክመቶች የሚመዘኑት በተቋማቱ ጥንካሬና ድክመት ነው። የመንግሥትን በሕዝብ ዘንድ ያለውን ቅቡልነት በዚሁ ልክ ይወስናሉ። መንግሥትም በላቀ አፈጻጸማቸው የመሸለሙ ምስጢር በእነዚህ ምክንያቶች ይመስለኛል።

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ለተቋማቱ የተሰጠው እውቅና የሚያስገኘው ፋይዳ አንደኛውና ዋናው ጥቅም ጠንካራና ዘመኑን የዋጀ ተቋማትን መገንባት ያስችላል። ከታሪክ እንደምናየው ጠንካራ ተቋማት ያሉት ሀገር በሁለንተናዊ እድገቱ ውጤታማ ይሆናል። ሁለተኛው ደግሞ ለብሔረ መንግሥት ግንባታው ቁልፍ ሚና ያለው መሆኑ ነው። ይህ ማለት ጠንካራ ተቋማትን መገንባት ጠንካራ ብሔረ መንግሥት እንዲመሠረት ያስችላል። ሶስተኛው ደግሞ በመሥሪያ ቤቶች መካከል መልካም የሥራ ፉክክር እንዲፈጠር በማድረግ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማስቻሉ ሲሆን፣ አራተኛው ደግሞ ተቋማቱ ራሳቸውን እንዲፈትሹ ዕድል መስጠቱ ነው። በዚህም ጠንካራ ጎኖቻቸውን የበለጠ ለማጠናከር፤ ድክመቶቻቸውን ደግሞ ለመቅረፍ ያስችላል።

**የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴው ግድብ እንደ ሀገር ግዙፍ እና የሀገርን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚወስን ታላቅ ግድብ ነው**

በርግጥ የሚሉት የታሪክ ተመራማሪው፣ የተሸለሙት መሥሪያ ቤቶች ሙሉ በሙሉ ክፍተት የለባቸውም ማለት አይደለም፤ ይልቁን ከሌሎች የተሻለ የሥራ አፈፃፀም ስላስመዘገቡ ነው ብለዋል።

በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በሥነ ዜጋ እና ሥነ ምግባር ትምህርት ክፍል የመልካም አስተዳደርና ልማት መምህር አዳፍረው አዳነ በበኩላቸው፤ ሰሞኑን በሀገራችን በመንግሥት ደረጃ የተከናወነውን “የኢትዮጵያ ተቋማት ስኬት ሽልማት” እንደዚህች ሀገር ዜጋ የሚሰማኝ ነገር ቢኖር በየዘርፉቹ መልካም ሊባሉ የሚችሉ የጅማሮ ስኬቶችን እውቅና ለመስጠትና ለማወደስ የተደረገ የሽልማት ሥነ ሥርዓት አድርጌ ነው ብለዋል። ለዚህም በምክንያት ያስቀመጡት፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ካላት እንጡራ ሀብትና የመበልፀግ ዕድል አንፃር የተመዘገቡት ስኬቶች ጅማሮ እንጂ ፍፃሜ አይደሉም ሲሉ ነው።

እርሳቸው እንደሚሉት ገና ብዙ ይቀረናል። መዳረሻችን እና ስኬታችን ከሀገር አልፎ ለአህጉራችን አፍሪካ ብሎም ለዓለም ማብራት እስኪችል ድረስ የመሥራትና የመለወጥ ጫፍ ሊኖረው ይገባል። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይህንኑ አፅንዖት ሰጥተው ሲናገሩ ተደምጠዋል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴው ግድብ እንደ ሀገር ግዙፍ እና የሀገርን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚወስን ታላቅ ግድብ ነው የሚሉት መምህር አዳፍረው፣ ለሕዳሴው ግድብ ያልተሰጠ እውቅና ለሌላ ለየትኛውም ተቋም ሊሰጥ አይችልም ብዬ አምናለሁ ይላሉ። የሕዳሴ ግድብን ግንባታ ከመጀመር አንስቶ እስካሁን ባለው ሂደት ውስጥ የገጠሙ በርካታ ተግዳሮቶች በሀገር ወዳድና ቁርጠኛ



ሰማኸኝ ጋሻው



አዳፍረው አዳነ

አመራሮች እንዲሁም የሀገር ፍቅር ስሜት በሰነቁ ሠራተኞች ዘንድ ብዙ ዋጋ የተከፈለበት እንደሆነ እውን ነው ሲሉም ያመለክታሉ።

እንደ የታሪክ ተመራማሪው ገለጻ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ማለት ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ክብሯ ነው ቢባል ማጋነን አይደለም። እንዲህም ሲባል ኢትዮጵያ በቀጣናው ያላትን በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አቅሟን የሚወስን መሆኑን አመላካች ነው። በተለይ በፖለቲካው ዘርፍ ኢትዮጵያ የቀጣናውን ጂኦፖለቲካዊ ሚዛን መቆጣጠር እንድትችል ያደርጋል።

ይህ ደግሞ ግብጽ መሠረት ያደረገቻቸውንና በዓባይ ወንዝ ላይ ኢ-ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም እንዲኖር የሚደነግጉ የቅኝ ግዛት ስምምነቶችን ውድቅ ከማድረግ ይጀምራል። በተለይም ሁለቱ የቅኝ ግዛት ውሎች ማለትም፤ እ.ኤ.አ በ1929 እና በ1959 የተፈረሙ ስምምነቶች ሙሉ በሙሉ ከግብጽና ከሱዳን ውጭ ያሉትን የተፋሰስ ሀገሮችን ጥቅም ያሳጡ ነበሩ። በተለይም ደግሞ የዓባይን 85 በመቶ ውሃ መጠን ለምትለግሰው ኢትዮጵያ ይህ ታላቅ ንቀት ነበር። በወቅቱ እንግሊዝ ሁለቱንም የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ማለትም ግብጽ እና ሱዳንን በቅኝ ግዛት ታስተዳድር ስለነበርና ሰፊ የሆነ የመስኖ እርሻ ስለነበራት የዓባይ የውሃ ፍሰት መጠን እንዳይቀንስ በማሰብ በእነዚህ ስምምነቶች አማካኝነት የዓባይን ውሃ ለሁለቱ ሀገራት ብቻ አከፋፍላለች ይላሉ።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ እ.ኤ.አ በ1929 በተደረገው ስምምነት ለግብጽ 48 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ እና በዓባይ ወንዝ ላይ የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን ሲሰጣት፤ ለሱዳን ደግሞ በበኩሏ 4 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ተሰጥቷ ነበር። እ.ኤ.አ በ1959 በተደረገው ስምምነት ደግሞ፤ ግብጽ የውሃ ድርሻዋን ወደ 55 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ከፍ ስታደርግ፤ ሱዳን በበኩሏ ወደ 18 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ድርሻ ተፈቅዶላት ነበር። ቀሪው 10 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ በትነት እና ሌሎች ምክንያቶች ሊባክን እንደሚችል ታሳቢ ተደርጓል።

ከዚህ እንደምናየው ይላሉ የታሪክ ተመራማሪው ሰማኸኝ፣ ከ11ዱ የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት ውስጥ 9ኙ በስምምነቶች ውስጥ አልተካተቱም ብቻ ሳይሆን ምንም ዓይነት በውሃቸው የመጠቀም መብት አልተፈቀደላቸውም። ይህ የሌሎች ሀገሮችን ጥቅም በመደፍጠጥ የራስን ሀገር ማዘመን ደግሞ የቅኝ ግዛት ሌጋሲ እሳቤ ነው።

ለዚህ ነው ከታሪክ አንፃር ስንመለከተው፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ የሕዳሴውን ግድብ በብቃት ስታጠናቅቅ አዲሱን የቅኝ ግዛት እሳቤ (Neocolonialism) በድል እንደተወጣች የምንቆጥረው። በተጨማሪም ከዚሁ ከፖለቲካዊ ጥቅሙ ሳንወጣ፤ ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሀገራት የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በማድረግ ያላትን ተሰሚነት ታጠናክራለች፤ ለሌሎች የላይኛው ተፋሰስ ሀገራትም ፍትሃዊ የዓባይ ውሃ አጠቃቀምን ታረጋግጣለች። በሌላ በኩል ለቅኝ ግዛት እሳቤ እና ሌጋሲ አራማጅ ለሆኑት ግብጽ እና ሱዳን የሕዳሴው ግድብ በስኬት መጠናቀቁ ሽንፈት ይሆናል ብለዋል።

በኢኮኖሚው ዘርፍ ደግሞ ለጎረቤት ሀገራት የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ፤ የዓሣ እና ተያያዥ ምርቶችን በማምረት፤ የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎቶችን በማስፋፋት ምጣኔ ሀብታችንን ለማነቃቃት ያግዛል ሲሉም አመልክተዋል።

በማኅበራዊ ዘርፉ ደግሞ በዋናነት የኢትዮጵያውያንን የእርስ በእርስ ግንኙነትን ማጠናከር መቻሉ ነው። እንደሚታወቀው ከዓድዋ ድል በኋላ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዐሻራውን ያሳረፈበት ክስተት የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ነው። ይህ ግድብ በአብሮነት የተንሰላሰልንበት ትልቅ ሰንሰለት ነው። ይህ ጠንካራ የአብሮነት መንፈስ ደግሞ ለብሔረ መንግሥት ግንባታው ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

ለዚህ ግድብ በሀብት፤ በጉልበት፤ በእውቀት፤ በጊዜና በሕይወት ጭምር ዋጋ ተከፍሎበታል። የተከፈለውን ዋጋ እጅግ ከባድ ካደረጉ ሁነቶች መካከል ደግሞ በዋናነት የቅኝ ግዛት ሥነ ልቦናዊ ውቅር ያላቸው የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ጣልቃ ገብነት ተጠቃሽ ነው። በነዚህ እጅግ ውስብስብ ፈተናዎች ውስጥ ሆኖ ግድቡን በስኬት ማጠናቀቅ የዓድዋ ድልን እንደ መድገም እቆጥረዋለሁ። ስለዚህ የታላቁን ሕዳሴ ግድብ መሸለም መላ ኢትዮጵያዊያንን እንደመሸለም እቆጥረዋለሁ።

መምህር አዳፍረውም ልክ እንደ ታሪክ ተመራማሪው ሰማኸኝ፣ የሕዳሴ ግድቡ ለኢትዮጵያውያን የኩራት ምንጭ ነው ይላሉ። የዚህ ግድብ ግንባታ በብዙ ፈተናዎችና ውጣውረዶች ውስጥ አልፎ ዛሬ ላይ የሲቪል ሥራዎችን በማገባደድ ለሀገራችን ከፍተኛ ተስፋን የሰነቀ የአሸናፊነትን መንፈስ ማላበስ እንደቻለም ያስረዳሉ። የሕዳሴ ግድቡ ከዚህ በተጨማሪ የአንድነትና የጋራ ተጠቃሚነት መርህን ማረጋገጥ የቻለ ነው ብለዋል።

ስለዚህ ለሕዳሴው ግድብ እንደተቋም እውቅና መስጠት ማለት የሀገሪቱ ሕዝቦች በአንድነትና በቁጭት ከተረፋቸው ላይ ሳይሆን ካላቸው ላይ ቀንሰው ላደረጉት አስተዋፅኦ እውቅና እና ክብር መስጠት ነው ብዬ አምናለሁ ሲሉም አመልክተዋል።

የሕዳሴ ግድቡን ጨምሮ ለተቋማቱ የተደረገው ሽልማትና እውቅና እንደ ሀገር ለመልማትና ለማደግ ያለንን ፍላጎትና አቅም እንደ መንግሥት ዋጋ የተሰጠው ቀዳሚ ተግባር እንደሆነ ማሳያ ነው ያሉት መምህር አዳፍረው፣ መንግሥት ለእነዚህ ተቋማት ሽልማት ሲሰጥ ትርጉሙ ዘርፈ ብዙ ነው ብለዋል። ይሄውም ተቋማቱን ከዚህ የበለጠ ለማትጋትና አደራ ለመስጠት ያለመና ሌሎች ተቋማትም ለሀገር ማበርከት ባለባቸው ልክ እንዲተጉ የማንቂያ ደውል እንደሆነም ገልጸዋል።

እንደ ምሁራኑ ገለጻ፤ ሌሎች ተቋማት ከዚህ ሽልማት ሊማሩ ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ የእነዚህን ተቋማት ልምድ በመቅሰም ለለውጥ መትጋት ነው። የሀገርን ልማት ለማረጋገጥ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ደግሞ ሌላው ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል በዚህ የእውቅና ሥነ ሥርዓት ያልተካተቱት መሥሪያ ቤቶች መልካም ተሞክሮዎችን ከተሸላሚዎች በመቅሰም ለቀጣይ ሥራቸው ስኬት እንዲተጉ፤ የሥራ አፈፃፀም ድክመቶቻቸውን ደግሞ እንዲገነዘቡ ያግዛቸዋል።

በሀገራችን ተቋማት ከአካላዊ ቁመናቸው ባለፈ ውስጣዊ አሠራራቸውን በማዘመንና ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ለትክክለኛ እድገት የድርሻቸውን እንዲወጡ የተቋማዊ መሻሻሎችን (Institutional Reforms) መንደፍ ይኖርባቸዋል። ተቋማዊ መሻሻሎች ወይም ተቋማዊነት ማለት እንደ ሀገር ያሉንን መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ሕጎችን የአሠራር ሥርዓቶችን እንዲሁም ባህላዊና ማህበረሰባዊ እሴቶችን የተቋማትን የግለሰቦችን እንዲሁም የቡድኖችን ባህሪ በአግባቡና ገዢ በሆነ መንገድ መተግበር ማለት ነው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# መክሊቷን ዘግይታ የተረዳችው ድምፃዊት

አስመረት ብስራት

ከፒያሳ ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ ሰሜናዊ ክፍል የሚገሰግሱት ኮስትር አውቶብሶች ለመድረሻቸው የናፈቁ ይመስላሉ። በፍጥነት ተከታትለው ጥቁሩን አስፓልት ሲገምሱ ለተመለከታቸው ዓይን ይስባሉ። በአግባቡ አሸብርቆ የተሠራው መንገድ የእንጦጦ ጋራን አሳምሮታል። ከዳር ዳር ተራራውን በሸፈነው ዛፍ መካከል እያቆራረጥን የኩሪፍቱ እንጦጦ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ደርሰናል።

አዳራሹ መግቢያ ላይ ቀያይ አበባን ይዘው የቆሙት ወጣት ሴቶች ቀኑ እውነትም የሴቶች ነው የሚያስብሉ ናቸው። አሚጎስ የተባለ የቁጠባና የብድር ህብረት ሥራ ማህበር ለሴቶች ቀን ባዘጋጀው መድረክ ላይ ነበር የተገኘው። በእለቱ የቁጠባ ማህበሩ አባላት፤ የተቋሙ ሠራተኞችና ተጋባዥ እንግዶች ተገኝተው ነበር። በእለቱ የሕይወት ልምዳቸውን ካከፈሉን ጠንካራ ሴቶች መካከል አንዷን ለሴቶች ዓምድ እንግዳ አድርጌ ይገፄላችሁ ቀርቤያለሁ። መልካም ቆይታ።

እናት መሆን ከሰጣት የእናትነት ውበት በስተቀር በመገናኛ ብዙኃን እንደምትታየው ዓይነት ናት። ደስ የምትል ተግባቢ ‹‹የኛ›› የተባለው ድራማ ላይ እንዳለችው ገፀ ባህሪ ሳይሆን ደርበብ ያለች እናት የምትመስል ቆንጆ ቅልብጭ ያለች ሴት ናት። በእለቱ ለተገኙት ታዳሚዎች የሕይወት ልምዷን ስታካፍል የተመልከትኳት ሴት ለምለም ኃይለሚካኤል ትባላለች። በእለቱ የማህበሩ አባላት ለሆኑና በተለያዩ አጋጣሚዎች ተጋብዘው በእንጦጦ ኩሪፍቱ ለተገኙት ሰዎች ስለራሷ እና በሕይወቷ ስላሳለፈቻቸው ውጣ ውረዶች በዚህ መልኩ ተናግራ ነበር።

በተወለደችባት ትንሽዬ የገጠር ከተማ ውስጥ ነው የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ያጠናቀቀችው። የአስረኛ ክፍል ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች ወደ መሰናዶ የመግቢያ ውጤት ብታገኝም በአጋጣሚ ቤታቸው የተገኘች ቆንጆ ዘናጭ የጤና ባለሙያን ስትመለከት እንደ እሷ ተቀጥሮ የመሥራት ፍላጎት ያድርባታል። በዚህም የመሰናዶ ትምህርቷን ትታ የግብርና ኮሌጅ ገብታ በእንስሳት ሳይንስ ተመረቀች። ምንም እንኳን የግብርና ባለሙያ ለመሆን ብትማርም የነፍሷ ጥሪ አላስቀምጥ ያላት ወጣት ተነስታ አዲስ አበባ መጣች።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ከተቀላቀለች በኋላ በቲያትሪካል አርት የመጀመሪያ ዲግሪ ሁለተኛ ዲግሪዋን ደግሞ ትያትር ፎር ዴቨሎፐመንት የሚል ትምህርት ተማረች። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከወጣች በኋላ የኛ የተባለውን የሙዚቃ ቡድን ተቀላቀለች።

ከሙዚቃ ቡድኑ በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ መድረክ ላይ የታየችው ሀገር ማለት ሰው ነው የሚል ሀገርን የወከለች ሴት ገፀ ባህሪን ወክላ ለብሔር ብሔረሰቦች ቀን የቀረበ ትያትር ተጫውታ ነበር። ከዚህኛው መድረክ በኋላ የኛ የሚል ለሰባት ዓመታት በሬዲዮ የተላለፈ ሙዚቃዊ ድራማ ላይ ተጫውታለች። በወቅቱ የጎዳና ልጅ ሆና ወንዳ ወንድ ገፀ ባህሪ ተላብሳ ለሰባት ዓመታት ያህል ሰርታለች።

ሁሉም ሰው በሕይወቱ የተሰመረለትን መስመር እንደሚጓዝ የምትናገረው ለምለም ስትወልድ በጣም ገጠር ከተባለች መብራት ከማታገኝ ከተማ መውጣቷ፤ ልጅነቷን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የገጠር ልጅ ማደጓ፤ ከዛም በኋላ የሞከረቻቸው የሄደችባቸው የሕይወት መስመሮች አንዱ ለአንዱ ድልድይ እየሆነ በስተመጨረሻ መክሊቷን አግኝታ በዛ ሙያ ውስጥ ተሰማርታ ትገኛለች።

በሕይወታችን የምንፈለገውን ባለማወቅ ሕይወታችን ትርጉም እንዳይኖረው እናደርጋለን የምትለው ለምለም እሷ አስረኛ ክፍል ጨርሳ በግብርና ትምህርት ዘርፍ የእንስሳት ሳይንስ ስትማር ዓላማዋ የነበረው ዘጠነኛ ክፍል እያለች በጣም ቆንጆ ወጣት ከጅማ ዩኒቨርሲቲ በግብርና ሙያ ተመርቃ በሥራው የተሰማራች ሴትን በማየቷ እንደ እሷ የመሆን ፍላጎት እንዳደረባት ትናገራለች።

ከዛ በፊት አትሌት ለመሆን ፈልጋ ሞክራ ያልተሳካላት ጊዜ የነበረ ቢሆንም በእንግድነት ቤታቸው የመጣችውን ወጣት ስታይ ግን እንደሷ መልበስ፤ እንደሷ ፀጉሯን ማስያዝ መፈለግ ጀመረች። ተመርቃ እንደወጣች በጣም ገጠር ውስጥ ስትመደብ መሥራት እንደማትችል ቤተሰቧን አስረድታ መክሊቷን ፍለጋ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት መጣች።

በወቅቱ ቲያትር መማር የፈለገችው በፊልም ስታያት የነበረችው አክሽን ፊልም የምትሰራውን አንጀሊና ጁሊ ለመሆን ነበር። አክተር የሚለውን ስም ትርጉም እንኳን በአማርኛ ሳታውቅ ነበር አክተር ለመሆን ትምህርት ቤት የገባችው። ሳይንሱን ስታወቅ ግን ትወና ሌላ ዓለም መሆኑን ተረዳች። በዩኒቨርሲቲ ለመጀመሪያ ዲግሪ አራት ዓመታትን ስትማር ቆይታ ስትጨርስ ሥራ የምትይዝ መስሏት የነበረ ቢሆንም ሥራ በቀላሉ እንደማይገኝ የተረዳችው ተመርቃ ሥራ መፈለግ ስትጀምር ነው። ሥራ ለማግኘት የተለያዩ ሙከራዎች ብታደርግም ለቲያትር ተማሪ የሚሆን ሥራ ማግኘት አልቻለችም ነበር።

ዘፈን እንደምትችል ወይም ዘፋኝ መሆን እንደምትችል አንድም ቀን አስባ አታውቅም ነበር። በልጅነቷ ሰንበት ትምህርት ቤት ከመዘመርዋ ውጭ ምንም ዘፈን ሞክራ አታውቅም ነበር። የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ላይ የአንድ ኮርስ ማሟያ ላይ ስትዘፍን የተመለከታት መምህር ዘፋኝ መሆን እንደምትችል ይነግራታል። እሷ ግን አንድም ቀን ዘፋኝ የመሆን ህልም ኖራት እንደማያውቅ ትናጋራ ችላ ብላ ታልፈዋለች።

ከዚህ ሁሉ በኋላ የተቀላቀለችው የኛ የተሰኘው ሙዚቃዊ ድራማ ላይ ትልቅ ደመወዝ እየተከፈላት መሥራት ጀመረች። ግብርናን፤ ትያትር፤ ተምራ የኛ ሙዚቃዊ ድራማ ላይ ለስባት ዓመት ስትሠራ ሕዝቡ ልብ ውስጥ ለመግባት በርካታ ጥረት አድርጋለች። ከገፀ ባህሪዋ ጋር ለመዋሃድ ጎዳና ላይ ወጥታ የጎዳና ልጆች ሁኔታን እስከማጥናት ደርሳ እንደነበር ትናገራለች። ከሰባት ዓመታት በኋላ በእድሜም እየበሰለች ስትሄድ ራሷን ለመሆን ህልሟን ለማግኘት የተለያዩ ራስን ማሳደጊያ ሥልጠናዎች ትወስድ ነበር።

“ሴትነት የሚኖርበት መንገድ፤ ሴትነት የሚቀነቀንበት መንገድ ሁሉ ጥያቄ ይፈጥርብኛል” የምትለው ለምለም ሴትነት ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ፤ ሴትነት ከሰዎች አስተሳሰብ አንፃር፤ በአጠቃላይ ከተለያዩ እይታዎች አንፃር ሲቃኝ በርካታ አተካራዎች ውስጥ ከውስጧ ጋር ብትገባም ሴት ወንድ ከሚል አስተሳሰብ ወጥታ ሰው መሆን በሚል አስተሳሰብ ራሷን ለመረዳት መታገል ጀመረች። የለምለምን የሕይወት ጥሪ ማወቅ፤ ለምለም ምን መክሊት እንዳላት ለመረዳት ጥረት ማድረግ ጀመረች። እራሷ ምን እንደምትፈልግ የእሷ መስመር የቱ እንደሆነ ለማጣራት ቆማ ውስጧን መመልከት ጀመረች።

በዚህ መካከል የኛ የተባለው ሙዚቃዊ ድራማ ለቀጣይ ሶስት ዓመታት ይቀጥላል እየተባለ ባልታሰበ ሁኔታ ፕሮጀክቱ ሲቋረጥ አስደንጋጭ ሁኔታ ውስጥ ገባች። በወቅቱ ዴይሊ ሜል የሚባል የእንግሊዝ ሀገር ጋዜጣ አምስት እስፓይስ ገርሎችን ለማቋቋም አምስት ሚሊየን ፓውንድ ወጣ ብሎ ዜና በመሥራቱ የተነሳ ምንም ቅድመ ሁኔታ ያልነበራቸው፤ የተሻለ ሕይወትን የተለማመዱ ወጣቶች እንዲበተኑ ሆነ።

በዚህም ምክንያት ከነበረችበት የሕይወት ደረጃ ዝቅ ማለት የግድ የሚል ወቅት መጣ። ከጥሩ ደመወዝ በድንገት የተነቀለችው ወጣት ኑሮን ዝቅ አድርጎ ለመኖር መልመድን እየሞከረች ነበር እናት የሆነችው። የመጀመሪያ ልጇን ከወለደች በኋላ ምንም ዓይነት ገቢ ሳይኖራት አጋሯ በሚያገኘው ገንዘብ ልጇንና እሷ በአነስተኛ ገቢ ለመኖር መታገል ጀመሩ። በወቅቱ አዲስ የእናትነት ልምምድ ውስጥ ገባች። እናት መሆን ብርቅ የሆነባት ወጣት ለአንድ ዓመት ከአምስት ወር ልጇን ብቻ እየተመለከተች አቅፋ መዋል ሥራዋ ሆነ።

ሙሉ ጊዜዋን ያለ ምንም እንቅስቃሴ ከልጇ ጋር የነበረችው ለምለም ክብደቷ ሰማንያ አራት ኪሎ ላይ ደረሰ፤ ከአዲስ እናትነት ጋር የሚመጣ ድባቴ ውስጥ ገብታ ደጅ መውጣት እስኪያሰጨንቃት ድረስ ቆይታ ነበር። ከዛ የሥነ ልቦና ባለሙያ በማነጋገር እራሷን በመቀበል ነገሮችን ማስተካከል እንደምትችል አመነች። ከሰማንያ አራት ኪሎ ወደ ሰባ ሁለት ለመውረድ ሁለት ወራትን ብቻ ነበር የፈጀባት። በመቀጠል የነበረቻትን መኪና ፍቃድ በማውጣት የትራንስፖርት አገልግሎት እንድትሰጥ አደረገቻት። የኢኮኖሚ ችግሮቿን በመቀነስ ቀስ በቀስ ወደ ቀደሞ አቋሟ መመለሷን ትናገራለች።

ከዛ በኋላ ገዳም የሚለውን ሙዚቃ ከአምስት ዓመታት በፊት ለቀቀች። በወቅቱ የየኛ ቡድን አባላት አብዛኞቹ ነጠላ ዜማቸውን ለቀው ስለነበር ያለምንም ችግር ገበያው ውስጥ ለመግባት አስችሏት ነበር። ነጠላ ዜማውም በወቅቱ ከፍተኛ የሚባል ሽያጭ ነበር ያስመዘገበው። ከእናትነት በኋላ ከዜሮ ተነስታ ከፍ ያለ ቦታ ደርሳለች።

ከነጠላ ዜማው በተጨማሪም ከጓደኞቿ አብሮ የሚሰራ ሥራ ላይ ትሳተፍ እንደነበርም ታስታውሳለች። ከነጠላ ዜማዎች ጎን ለጎን አልበም ለመሥራት ከኤሊያስ መልካ ጋር የተገናኘችበትም አጋጣሚ የሙዚቃ መስመሮች እንደዘረጋላት ትናገራለች። አሁን አልበም ጀምራ ዘጠኝ ዜማዎችን ሰርታለች። በቅርቡም ሙሉ አልበም እንደምታስመርቅ ትናግራለች።

“የሕይወት መስመሬን ባለማወቄ በተቀደደልኝ ቦይ ነበር የምፈሰው። አንድም ቀን የራሴን ግብ አስቀምጬ አላወቅም ነበር። የሕይወት ግቤ ጠፍቶ ራሴን ጥዬ የነበረም ሲሆን አሁን በሙዚቃ መስመር ውስጥ ተደላደዬ እየኖርኩ ነው።”


ሁለተኛ ልጄን ከወለደኩ በኋላ በርካታ ጫናዎች ላይ በነበርኩበት፤ ብዙ ነገር ሳልችል ቀርቼ የሚያስችል አምላክ እንዳለ ያየሁባት ቆንጆዋን ልጄን ማያ ብያታለሁ። ልጆች የራሳቸውን በረከት ይዘው ይመጣሉ የሚባለው እውነት ነው፤ ልጆች በረከቶች ናቸው። ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው።

የልጆቼ እናት ለመሆን አልበም አቁሜ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አስተዋዋቂ ለመሆን አስቤም ነበር። ሁለተኛ ልጄን ስወልድ ሙዚቃ መስማት አቁሜም ነበር። ግን ሁሌ ሙያ መቀያየር መፈለግ ውስጥ ተጠምጄ ቢሆንም እኔ የምችለው መዝፈን ነው። መክሊቴን ያወኩት በሰላሳ ምናምን ዓመት እድሜዬ ላይ ነው።

“ባህር ዳር ለመሄድ የህዋሳ መኪና ተሳፍሬ የተንገላታሁ ሰው ነበርኩ። አሁን ግን ስኬታማ የሆኑ ሰዎችን መመልከት ማየት ማዳመጥ ጀመርኩ። ሰዎች ሙዚቃዬን ይወዱታል ሙዚቃዬ ለሰዎች ተደራሽ ይሆናል። የተሰጠኝ መክሊት ሙዚቃ ነው ብዬ አሁን አልበሜን ሰርቼ ለመጨረስ በቃሁ” ብላለች።

“እኔ የሄድኩበት መንገድ ከባድ የነበረ ቢሆንም፤ መወለዴ ከብዶኝ ነበረ ቢሆንም የእናትነት ኃላፊነት ከባድ ቢሆንም አልፈዋለሁ። እናትነትን በተገቢው መንገድ ችዬበታለሁ። እስከዛሬ ህልሜን ሳለውቅ ቆይቻለሁ፤ አሁን ህልሜን አውቄ ላሳይ ነው። አልበሜም በቅርቡ ይደርሳል፤ በእኔ ሕይወት መስመር ላይ ቆም ብዬ ስመለከት ካርጎዬን ስቼ ነበር። አሁን ሁሉ አልፏል ሙሉ ሴት ነኝ” ብላለች።

ዛሬ ስኬታም ዘፋኝ የሆነችው ይህች ሴት በበርካታ የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ማለፏን ስትናገር ማንም ሰው የሚወደውንና የሚፈልገውን መሥራት ከቻለ ለስኬት ቅርብ ነው የሚል መልእክት አስተላልፋለች እኛም በዚሁ መልእክቷ ተሰናብተናል። ቸር ይግጠመን።



ሰምሰም ኃይለሚካኤል

**በሕይወታችን የምንፈለገውን ባለማወቅ ሕይወታችን ትርጉም እንዳይኖረው እናደርጋለን**

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

በትምህርትና በእውቀት የተደገፈ አልቃሽነት ያስፈልጋል በማለት አዲስ የለቅሶ ዜማ ተደርሶ በለቅሶ ላይ ሊውል ነው። የማስለቀስ ልምዳችሁን በስልጠና አዳብሩ የተባሉት የመንደር አልቃሾቹም፤ ገሚሱ አሻፈረኝ በማለት ተቃውሟል፤ ገሚሱ ደግሞ ተማሩ ካላችሁን የምንማረው እየተከፈለን ካልሆነ በማለት ተቃውሟቸውን አሰምተዋል። አዲስ ዘመን ድሮ ወደ 1963ዓ.ም መልሶ ይህን ያስነብበናል። አውቶቡሱ ተገልብጦ ሰዎችና 58 በጎች ተዳጡ። ከሁለቱ የመረጃ ትውስታዎች ጋር "አንድ ጥያቄ አለኝ" ከተሰኘው የጳውሎስ ኞኞ ደብዳቤዎች፤ በምልሰት ብዙ ጉዳዮችን እንመለከታለን።

### አውቶቡስ ተገልብጦ ሁለት ሰዎች ሞቱ 58 በጎች ተዳጡ

የአንበሳ አውቶቡስ ከዛፍና ከገደል ተጋጭቶ፤ 4 ቤት ጥሶ ገብቶ በተፈጠረው አደጋ፤ ሁለት ሰዎች ወዲያውኑ ሞተዋል። እንዲሁም በደረሰው አደጋ 22 ሰዎች በጠና ሲቆስሉ፤ 58 በጎች አልቀዋል።

አደጋው የተፈጠረው ከእንጦጦ ተራራ ላይ የሚሽቆለቆል ቁጥር 15 ሺህ 125 የሆነ የአንበሳ አውቶቡስ ከሹፌሩ ቁጥጥር ውጪ በመሆኑ፤ በአደጋ ላይ እንዳለ በ1 ሺህ ሜትር ርቀት ተጉዞ ከገደል፤ ከጉድጓድና ከቤት ጋር እየተጋጨ አሳዛኝ ድርጊት ከተፈጠረ በኋላ መሆኑን ከስፍራው የነበሩት ሰዎች አመልክተዋል።

...

(አዲስ ዘመን መስከረም 1 ቀን 1966ዓ.ም)

### አዲሱን የለቅሶ ዜማ የመንደር አልቃሾች ተቃወሙ

የቤተሰብን ጤንነትና አካል እንዲጠብቅ ተብሎ በፀሎት መልክ የቀረበውን አዲሱን የሀዘን ዜማ አንዳንድ የመንደር አልቃሾች መቃወማቸውን አቶ አብረሃም መኮንን በኢትዮጵያ መንበረ ፓትሪያርክ፤ የወጣቶች አንድነት ማዕከላዊ ፅ/ቤት ዋና ፀሐፊ አስረዱ።

አዲሱን የለቅሶ ዜማ የመንደር አልቃሾች ኮርስ ወስደው እንዲያጠኑ ተጠይቀው ፍቃደኞች አለመሆናቸውን ዜና ሰጪው ተናግረዋል።

አዲሱ ዜማ አንድ ሰው ሲሞት በህብረት ዝማሬ እየተዜመ ሙታንን ለመሸኘት የሚያስችል ነው።

በተለይ አንድ ሰው በሞተ ጊዜ የሟች ቤተሰቦች ደረት በመደለቅ፣ ከመሬት በመፈጥፈጥ፣ ፊት በመንጨት የሚደርስባቸውን ከባድ ጉዳት የሚያስወግድና ስርአትና መልክ ያለው መሆኑን አቶ አብረሃም ገልጠዋል።

በዚህ መሰረት ሰባት ዓይነት ልዩልዩ በህብረት የሚዜሙ የለቅሶ ዜማዎች ተዘጋጅተውና ተፈልስፈው ይገኛሉ።

ዜማዎቹን የደረሱት አቶ አብረሃም ሲሆኑ እነዚህኑ ዜማዎች በኮርስ መልክ የመንደር አልቃሾች እንዲያጠኑ 8 ያህል አልቃሾች ማነጋገራቸውን ዜና ሰጪው ተናግረዋል።

ከስምንቱ አልቃሾች ሁለቱ ወንዶች ሲሆኑ ጥቂቶቹ አልቃሾች ዜማውን ለማጥናት ኮርስ ከገባን ዜማውን እስከናጠናቅቀው ድረስ በወር 25 ብር ክፈሉን በማለት አቶ አብረሃምን የጠየቁ መሆናቸውን ዜና ሰጪው አስረድተዋል።

ቀጥለውም ‹‹ካነጋገርኳቸው ጥቂቶቹ የመንደር አልቃሾች ዘንድ ብዙ ወቀሳ ደርሶብኛል። ብላችሁ ብላችሁ በእንጀራችን ገባችሁ አሉኝ። ቄሶች በአንድ በኩል ያወግዛሉ። እኛ ስራችን ነው በማለት ተቃውሟቸውን ገለጡ። ኮርስ ግቡና በወር 5 ብር ልክፈላችሁ አልኳቸው 25 ብር ካልሆነ ብለው ሀሳቤን ሳይቀበሉ ቀሩ›› ሲሉ አቶ አብረሃም ተናግረዋል።

አዲሱ የልቅሶ ዜማ ሙታንን እንዴት መሸኘት እንደሚገባ ትምህርትና ምክር የሚሰጥ መሆኑ ታውቋል። ይህም ዜማ ካሁን በፊት በደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ዜማውን ባጠኑ ተማሪዎች በቴያትር መልክ ተዘምሮ ታይቷል። በሁለቱም ቀኖች የተገኘው ህዝብ በብዛት የሚቆጠር መሆኑንና በተመለከተው ህዝብ መደገፉን አቶ አብረሃም ተናግረዋል። አሁን የመንደር አልቃሾች ዜማ ግን ሥርዓት የሌለው ነው ሲሉ ነቅፈዋል።

አቶ አብረሃም የመጨረሻ ማብራሪያቸውን ሲሰጡ ‹‹ያሁኑ የአልቃሾች ዜማ ወንዱና ሴቱ ተለይቶ አይነገርበትም። የሞተችው ሴት የሆነች እንደሆነ ለወንድ ያለቅሱበታል፤ ሟች አርበኛ የሆነ እንደሆነም አቶ እገሌ እህል ሲያመርት፤ እርፍ ሲይዝ እንዲህ አልነበረም ተብሎ ሙሾ ይቆምበታል። በጠቅላላ ዜማው ሥርዓት የሌለው ነው። ነገር ግን በህብረት እየተዘመረ የሚዜመውን አዲሱን የለቅሶ ዜማ በአልቃሾች ቢጠና ጥቅሙ እንደሚያመዝን አንጠራጠርም›› ብለዋል።

(አዲስ ዘመን ጋዜጣ መስከረም 7 ቀን 1963 ዓ.ም)

### አንድ ጥያቄ አለኝ

-አዘጋጅ ጳውሎስ ኞኞ

*የአዲስ አበባ ትራፊክ ክፍል ከባድ ቁጥጥር ጀምረናል ሲሉ በራዲዮ የተናገሩትን ሰምቼ ነበር። ቁጥጥሩ ግን ምን እንደሆነ አላየሁም። ለመሆኑ አንተ አይተሃል?

-ኸረ እኔም አላየሁም። ሲሉ ግን ሰምቻለሁ።

(አዲስ ዘመን ታህሳስ 10 ቀን 1966ዓ.ም)

*የሩጫ ስሜት አድሮብኝ የቸገረኝ ነገር ጫማና ቱታ ነው። የምገዛበትም የለኝምና ምን ይሻለኛል?

(መለሰ ጌታቸው)

-ያለ ጫማና ቱታ መሮጥ ይቻላል። እንዲያው አበበ ቢቂላ ሮም ላይ ያሸነፈው ያለጫማ ሩጦ ነውና ሰበብ ሳታበዛ ትሮጥ እንደሆን ሩጥ።

*ድሮ እሷ እወድሃለሁ ስትለኝ እኔ አልወዳትም ነበር። አሁን እኔን ፍቅር ብን ሲያደርገኝ እሷ ደግሞ ገሸሽ ታደርገኝ ጀመር። ጀነንም ያደርጋታል። እንዴት ወደነበረችበት ልመልሳት እችላለሁ?

( ከበደ ለማ)

-"የሷ ፍቅር አልቆ የኔ ሲጀመር፤

ሐዲዲም ፋዲዲም ያደርገኝ ጀመር" ይል ነበር የድሮ አዝማሪ። አንተም የያዘህ አባዜ እስኪለቅህ ድረስ እንዲያው ዝም ብለህ ኑር እንጂ አንዴ የጠላችህን ልጅ እንደድሮው ለመመለስ አትችልም።

*ወንድ ለምን ጡት አያወጣም?

(ወርቅነሽ አስፋው)

-እንደ እናንተ ትልቅ አይሆንም እንጂ ማውጣቱንስ ያወጣል። ያንዳንዱማ የተበደለች ልጃገረድ ጡት የሚያህል ያለው አለ።

*ከዚህ በፊት ስለ አልአዛር ጠይቄህ ስለየቱ አልአዛር ብለሽኝ ነበር። ከሀብታሙ ከነዌ ደጃፍ ወድቆ ይለምን ስለነበረው አልአዛር ንገረኝ።

( ፋንታሁን ቱሉ)

-ስለሱማ አዲስ ኪዳን ውስጥ አንብብ። ከዚያ የተለየ እኔም የማውቀው የለም።

(አዲስ ዘመን ሚያዚያ 12 ቀን 1966ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ቲክቶክን ማገድ ለምን ፈለገች? እገዳውስ ተግባራዊ የሚሆነው መቼ ነው?

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲከኞች አዲስ ረቂቅ ሕግ አውጥተው ቲክቶክ መታገድ አለበት አሊያ ደግሞ ባለቤቱ የቻይናው ኩባንያ ሊሸጠው ይገባል የሚል ክርክር ገጥመዋል።

የቪዲዮ ማጋሪያ የሆነው መተግበሪያ በመላው ዓለም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተጠቃሚዎች አሉት።

ነገር ግን የደንበኞቹ የመረጃ ደኅንነትን እየጠበቀ አይደለም፤ ከቻይና መንግሥት ጋር ግንኙነት አለው የሚሉ ክሶች ይቀርቡበታል።

ከሁለቱም የአሜሪካ አውራ ፓርቲ የተውጣጡ ፖለቲከኞች አዲስ ያረቀቁት ሕግ የቲክቶክ ባለቤት የሆነው ባይትዳንስ መተግበሪያውን ቻይናዊ ላልሆነ ኩባንያ ካልሸጠ ይዘጋል ይላል።

ሕግ አውጪዎቹ ቲክቶክ በአሜሪካ የሚገኙ 170 ሚሊዮን ደንበኞችን መረጃ ለቻይና መንግሥት አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል የሚል ስጋት አላቸው።

ቲክቶክ ግን የውጭ ሀገር መረጃ ለቻይና መንግሥት አሳልፌ አልሰጥም ሲል ያስተባብላል።

የአሜሪካ የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ባለፈው ሳምንት በ352 የድጋፍ ድምፅ እና በ65 ተቃውሞ ሕጉን አፅድቋል።

አሁን ረቂቅ አዋጁ ወደ ላይኛው ምክር ቤት (ሴኔት) ተሸጋግሯል። ነገር ግን ሴኔቱ እንደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ሕጉን በቀላሉ ያፀድቀዋል የሚል ግምት የለም።

አብዛኞቹ የሴኔት አባላት ሕጉን ይደግፉታል ወይ? የሚለው ጥያቄ ግልፅ ምላሽ አላገኘም።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ሕጉ በሴኔቱ ከፀደቀ ፊርማቸውን እንደሚያሰፍሩበት ተናግረዋል።

አዋጁ በሴኔቱ ፀድቆ የፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ፊርማ ካረፈበት፤ ባይትዳንስ ቲክቶክን ለመሸጥ የስድስት ወራት ዕድሜ ይሰጠዋል፤ ካልሆነ ከአሜሪካ ገበያ ይታገዳል።




ቲክቶክ አሜሪካ ውስጥ ታገደ ማለት ተጠቃሚዎች መተግበሪያውን ከሚያወርዱበት የአፕ ስቶር እና የጎግል ፕሌይ ይወገዳል ማለት ነው።

ረቂቅ አዋጁ "በውጭ አካላት የሚመሩ መተግበሪያዎችንም" አሜሪካ ውስጥ አፕዴት ማድረግ እና መጠገን አይቻልም ይላል።

ቲክቶክ አዲሱን ረቂቅ አዋጅ በጥብቅ እያወገዘው ነው።

የቲክቶክ ሥራ አስኪያጅ ሹ ዚ ቺው፤ ረቂቅ አዋጁ "ለሌሎች ማኅበራዊ ሚድያ የበለጠ ኃይል መስጠት ነው" አልፎም በሺዎች የሚቆጠሩ አሜሪካውያንን ከሥራ ውጪ ማድረግ ነው ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

ባይትዳንስ፤ ቲክቶክን መሸጥ ከፈለገ ከቻይና መንግሥት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል። ነገር ግን ቤይጂንግ ይህን እንደማታደርግ እያስጠነቀቀች ነው።

አሜሪካ የሚገኙ አንዳንድ የቲክቶክ ተጠቃሚዎች አዲሱን ረቂቅ አዋጅ እየተቃወሙት ይገኛሉ።

ቲክቶክ 170 ሚሊዮን የሚሆኑ በአሜሪካ የሚገኙ ተጠቃሚዎቹ ወደ ግዛቶታቻቸው ተወካዮች ደውለው ረቂቁን ሕጉን ውድቅ እንዲያደርጉት እንዲጠይቁ መክሯል።

ቲክቶክ ሕንድ ውስጥ ታግዷል። ሕንድ የቲክቶክ ትልቋ ገበያ ነበረች። ነገር ግን በአውሮፓውያኑ 2020 መተግበሪያውን አግዳዋለች።

መተግበሪያው በኢራን፣ በኔፓል፣ በአፍጋኒስታን እና በሶማሊያ ጥቅም ላይ እንዳይውል እግድ ተጥሎበታል።

በዩናይትድ ኪንግደም ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞች እና የፓርላማ አባላት በሥራ ስልካቸው ቲክቶክን እንዳይጠቀሙ ባለፈው ዓመት ተነግሯቸዋል።

የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽንም በተመሳሳይ በሥራ ስልክ ቲክቶክን መጠቀም አግዷል።

ቢቢሲ በደኅንነት ስጋት ምክንያት ሠራተኞቹ ከድርጅቱ የተሰጣቸውን ስልክ ተጠቅመው ቲክቶክን እንዳይገለገሉ ከልክሏል።

የቲክቶክ ዋናው መሣሪያ አልጎሪዝም (ስልተ ቀመር) ነው።

ይህ መተግበሪያው የተጠቃሚዎችን ታሪክ ተመልክቶ የትኛውን ዓይነት ይዘት ይወዳሉ የሚለውን የሚለይበት ዘዴ ነው።

ወደ ቲክቶክ ሲገቡ ከላይ ሦስት ንዑስ ርዕሶችን ያገኛሉ። ፎሎዊንግ፣ ፍሬንድስ እና ፎር ዩ ይባላሉ።

ፎሎዊንግ እና ፍሬንድስ ተጠቃሚዎች ከሚከተሏቸው ሰዎች እና ከጓደኞቻቸው የሚያገኟቸው ይዘቶች ናቸው።

ፎር ዩ የተሰኘው ደግሞ በራሱ መጥኖ ተጠቃሚዎች ይህን ይዘት ይወዱታል በሚል የሚለቀቅ ነው።

ተቺዎች ቲክቶክ ከሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያዎች በላይ የተጠቃሚዎችን መረጃ ይሰበስባል፤ ለዚህም ነው የተመረጡ ይዘቶችን የሚያቀርበው ይላሉ።

የተጠቃሚዎች አድራሻ፣ የሚጠቀሙበት ስልክ፣ የሚወዷቸው ይዘቶች እና ሲፅፉ የሚያሳዩት ባሕሪን ይሰበስባል የሚል ትችት ያቀርባሉ።

ነገር ግን ሌሎች እንደ ፌስቡክ እና ኢንስታግራም ያሉ ማኅበራዊ ሚዲያዎችም ይህን በማድረግ ይታወቃሉ።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በከተማዋ የሚሠሩ ፕሮጀክቶች የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን ያማከሉ ናቸው

**ዓስማሁ ግዛው**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማዋን ገጽታ የሚቀይሩና ማራኪ ውበትን ማላበስ የሚችሉ የልማት ሥራዎች በስፋት በመሠራት ላይ ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል ፓርኮች፣ ሙዝየሞችና ለኅብረተሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት የሚችሉ ስፍራዎች ዋነኞቹ ናቸው። እነዚህ ቦታዎች በከተማዋ የሚስተዋለውን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ፍላጎት መጨመርን ተከትሎ፣ ግንባታ ሲያካሂዱ ፍላጎቶቹን ያገናዘበና እነሱን ያካተተ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ስፖርት ምክር ቤት አስታውቋል።



**አቶ በላይ ደጀን**

የስፖርት ምክር ቤቱ ሰሞኑን 14ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን አካሂዶ በከተማዋ የተሠሩና መሠራት የሚገባቸውን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታና ሌሎች ጉዳዮችን ገምግሟል። በዚህም መሠረት የ2015 ዓ.ም እቅድ አፈጻጸም ሪፖርትና የ2016 ዓ.ም እቅድ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት ሊፀድቅ ችሏል። ከቀረቡትና ውይይት ከተደረገባቸው ዋና ዋና ነጥቦች መካከል የስፖርት ትምህርትና ስልጣና፣ የማህበረሰብ ስፖርት፣ የስፖርት ማህበራት፣ የስፖርት ውድድሮች፣ ከስፖርት ቤተሰቡ ጋር ለመሥራት የተደረገው ጥረትና የማዘውተሪያ ስፍራዎች ይገኙበታል።

በምክር ቤቱ ቀረበው ውይይት ከተደረገባቸው ነጥቦች መካከል በከተማዋ የሚገኙ ማዘውተሪያዎች ቀዳሚውን ቦታ ይይዛሉ። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በጥቅሉ 1236 የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን 741 ቦታዎች ባለፉት 5 ዓመታት የተሠሩ እንደሆነም ተመላክቷል። ከነዚህም ውስጥ በ2015 ዓ.ም ከመደመር ትውልድ መጽሐፍ ሽያጭ ከተገኘው ገቢ 13 የወጣቶች ስፖርት ማዘውተሪያና የሕፃናት መጫወቻ ስፍራዎች ሊገነቡ ችለዋል። ይህ ዘንድሮም ተጠናክሮ በመቀጠል በተጋመሰው የበጀት ዓመት 38 የሚደርሱ የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች ተገንብተው ለአገልግሎት ክፍት ሆነዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ስፖርት ምክር ቤት ተቀዳሚ ዓላማ ለኅብረተሰቡ ምቹ፣ በቂና ሁሉን ያማከለ የስፖርት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ በመሆኑ፣ ይህን እውን ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እንደተሠሩና ተጨማሪ ሥራዎችን ለመሥራትም እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑ ተጠቁሟል። የኅብረተሰቡ የስፖርት ጠቀሜታ ግንዛቤ እየጨመረ በመምጣቱ ያለው የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራና ፍላጎቱ ሊጣጣም ባለመቻሉ፤ ይህን ክፍተት ለመድፈን በመንግሥት፣ በስፖርት ምክር ቤቱና በበጎ ፍቃደኛ ባለሀብቶች ትብብር እነዚህን ስፍራዎች ገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት ሊደረጉ ችለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ትላልቅና ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ያሏቸው፣ የከተማዋ ፕሮጀክቶች የሚታየውን ከፍተኛ ፍላጎት በተወሰነ መልኩ ለመቅረፍ የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራን አካተው እየተገነቡ እንደሆነም ተጠቅሷል። የዓድዋ መታሰቢያ ሙዝየምና የሴቶች ተሀድሶና አእምሮ ማበልጸጊያ ማዕከል ለማሳያነት ቀርበዋል። እነዚህ ቦታዎች በውስጣቸው ጂምናዝየሞችንና የተለያዩ መጠን ያላቸውን ሜዳዎች በመያዝ ተሠርተው ሊጠናቀቁ ችለዋል። ይህንኑ ጅምር በማስቀጠል በቀጣይ የሚሠሩ የከተማዋ ፕሮጀክቶች የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራን አካተው እንዲገነቡ ምክር ቤቱ በልዩ ሁኔታ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

የሚሠሩ የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች ሁሉንም ስፖርት ፌዴሬሽንና አሶሴሽን ያማከለ ሆነውና ይበልጥ ውጤታማ የሚያደርጉ ስፖርቶች የሚገኙባቸውን ክፍለ ከተሞች መሠረት በማድረግ ሲሆን፤ ይህም ቀጣይነት እንዳለው ተጠቁሟል።

የስፖርት ምክር ቤቱ ምክትል ሰብሳቢ አቶ በላይ ደጀን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን የማስፋፋት፣ የማልማት፣ ተጀምሮ የነበሩትን ማጠናቀቅና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በጊዜው ማጠናቀቅ የምክር ቤቱ ተቀዳሚ ሥራ መሆኑን ጠቁመዋል። ለዚህም በከተማዋ እየተሠሩና ተሠርተው የተጠናቀቁ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ መሆናቸውን ተናግረዋል። መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በማልማት የወጣቶችንና የስፖርት ቤተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ላይ በስፋት እየተሠራ እንደሆነም አስረድተዋል።

የሚገነቡት ትልልቅ ፕሮጀክቶች፣ አዳዲስ ሆቴሎችና የመዝናኛ ስፍራዎችም የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎችን አካተው እንዲገነቡ እየተደረገ መሆኑን አክለዋል። ሰፊውን የኅብረተሰብ ፍላጎት ለማሟላት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከትምህርት ሰዓት ውጪ ለአካባቢው ኅብረተሰብ አገልግሎት እንዲሰጡም እየተሠራ ነው።

በከተማዋ የሚገኙ የተለያዩ ፌዴሬሽኖችና አሶሴሽኖች ውድድርና ስልጠና የሚሰጡበት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተሠርተው ሊጠናቀቁ እንደቻሉ የተገለጸ ሲሆን፤ በከተማ አስተዳደሩና በመንግሥት ድጋፍ በተለያዩ የከተማዋ ስፍራዎች ጥራታቸውን የጠበቁና ሁሉንም ያማከሉ ማዘውተሪያዎች ተገንብተው የማረጋገጫ ካርታንም ማግኘት እንደቻሉ አቶ በላይ ጠቁመዋል።

ካለው ከፍተኛ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ፍላጎት አኳያ መንግሥት ብቻውን ፍላጎቱን ሊያሟላ የማይችል በመሆኑ የሌሎች አካላት እገዛና ድጋፍን ይፈልጋል። በዚህም ላይ ለውጦች እንዳሉና ባለሀብቶች እገዛዎችን በማድረግ ብዙ ማዘውተሪያዎችን እየገነቡና እያደሱ እንደሆነ ተገልጿል። በዚህም 30 የሚደርሱ የማዘውተሪያ ስፍራዎች በበጎ ፍቃደኞችና ባለሀብቶች ትብብር ሊገነቡ ችለዋል። በተጨማሪም ሁለት ዓለም አቀፍ ደረጃን ያሟሉ የማዘውተሪያ ስፍራዎችን ማሻሻያ በማድረግ ለአገልግሎት ክፍት ሊደረጉ ችለዋል። 10 የማዘውተሪያ ስፍራዎች ሀገር አቀፍ ደርጃን የጠበቁ እንዲሆኑ ተደርገው መሻሻላቸውም ተጠቅሷል።